# አዲስ ዘመን

እናድ

ረቡዕ 82ኛ ዓመት ቁጥር 039 ጥቅምት 9 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ - ገበዮ ገብሬ

## “የውጭ ምንዛሪ እገዳው ተኪ ምርቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ መልካም እድል ይፈጥራል”

**አቶ ክቡር ገና**
**የምጣኔ ሃብት ባለሙያ**

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተወሰኑ ምርቶች ላይ የጣለው የውጭ ምንዛሪ እገዳ ከውጭ ይገቡ የነበሩ ምርቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ መልካም እድል ሊፈጥር እንደሚችል የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ክቡር ገና ገለጹ።

የፓን አፍሪካ የንግድ እና የኢንዱስትሪ ምክር ቤት ዋና ዳይሬክተር አቶ ክቡር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተወሰኑ ምርቶች ላይ የተጣለው የውጭ ምንዛሪ እገዳ እየጨመረ ያለውን የዋጋ ንረት ያረጋጋል። ተተኪ ምርቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ምክንያት ይሆናል።

ብሔራዊ ባንክ 38 ምርቶች ላይ ላልተወሰነ ጊዜ የውጭ ምንዛሪ እገዳ መጣሉን ተከትሎ ሀገር ውስጥ ያሉ የፋብሪካ ባለቤቶች አስፈላጊ ናቸው ብለው የገመቱትን በሀገር ውስጥ ለማምረት የሚሞክሩበት አንድ ምክንያት ሊሆን ይችላል ነው ያሉት።

ድጋፍ ከተሰጠ እና እገዛ ከተደረገ የሀገር ውስጥ አምራቹን በማነሳሳት ከውጭ ይገቡ የነበሩና የታገዱ ምርቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ የሚያደርግ ጥሩ ምክንያት ይሆናል ብዬ እገምታለሁ ብለዋል።

የቅንጦት እቃዎች ዋጋ በየጊዜው የሀገሪቱ የዋጋ ግሽበት ላይ ተጽእኖ እያሳደረ መሆኑን በመጠቆምም፤ ለነዚህ እቃዎች ግዢ ይውል የነበረው ገንዘብ ለልማት እና እሴት ጨምረው ለሚወጡ ዕቃዎች የሚውል በመሆኑ መልካም ነው ብለዋል።

“የውጭ ምንዛሪ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









## የሰላም ውይይቱ እንዲሳካ አሸባሪው ሕወሓት ትጥቅ መፍታት ይኖርበታል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በአፍሪካ ኅብረት መሪነት በአሸባሪው ሕወሓት እና በመንግሥት መካከል የሚደረገው የሰላም ውይይት ስኬታማ እንዲሆን ሕወሓት ትጥቅ መፍታት አለበት ሲሉ የፖለቲካ ምሑር አሳሰቡ፡፡

ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና ተመራማሪ አቶ ሱራፌል ጌታሁን፤

የሰላም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ሀገራዊ ምክክሩን አካታች ለማድረግ እያንዳንዱ የኅብረተሰብ ክፍል የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ጥሪ ቀረበ

- በአጀንዳ ቀረጻ ላይ ከ1 ሺህ 300 ወረዳዎች የተውጣጡ ተወካዮች ይሳተፋሉ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ ምክክሩን አካታች ለማድረግ እያንዳንዱ ዜጋ እና ቡድን የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ጥሪ አቀረበ:: በአጀንዳ ቀረጻ ላይ ከ1 ሺህ 300 ወረዳዎች የተውጣጡ ተወካዮች እንደሚሳተፉም ተጠቁሟል::

የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ኮሚሽኑ የተሰጠውን

ሀገራዊ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ

## መንግሥት በትግራይ ሰብዓዊ ርዳታ በተሳለጠ ሁኔታ እንዲደርስ በቂ ዝግጅት አድርጓል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት በትግራይ ክልል የሰብዓዊ ርዳታ በተሳለጠ ሁኔታ እንዲቀርብ ዝግጅት ማድረጉን አስታወቀ።

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

በትግራይ ክልል የሰብዓዊ አቅርቦት እና አገልግሎት ማስጀመርን በተመለከተ መግለጫ ያወጣው የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በትግራይ ክልል ከሰሞኑ የተወሰኑ ከተሞች መቆጣጠሩን ተከትሎ የተቀናጀ የሰብዓዊ ድጋፍ እንደሚቀርብ ገልጿል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባወጣው መግለጫ፤ ሠራዊቱ በከተሞች አካባቢ የሚካሄዱ ውጊያዎችን ለማስወገድ ጥረት ማድረጉንም አውስቷል።

መንግሥት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## የ12ኛ ክፍል የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች ፈተና በሰላማዊ ሁኔታ እየተሰጠ ይገኛል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የ12ኛ ክፍል የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች ፈተና ከትናንት ጀምሮ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች በሰላማዊ ሁኔታ በመሰጠት ላይ መሆኑ ተገለጸ፡፡ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እና ሚኒስትር ዴኤታው ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ሂደትን ጎብኝተዋል፡፡

በጉብኝታቸውም ተማሪዎች በተረጋጋ ሁኔታ ፈተናውን እየወሰዱ

የ12ኛ ክፍል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







የጣና ፍረም ተጨማሪ የቱሪዝም እድል ሆኗል



ገጽ 3

# የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የቡና ወጪ ንግድ ድርሻ ለማሳደግ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል

**ምሕረት ሞገስ**

ሚዛን አማን፡- የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከቡና ወጪ ንግድ ያላቸው ድርሻ ከሦስት ዓመት ወዲህ እየቀነሰ በመምጣቱ ተሳትፏቸውን ለማሳደግ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ተገለፀ፡፡

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በሚዛን አማን ከተማ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የቡና ምርት ልማት ግብይት ሲምፖዚየም ተካሂዷል።

የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኮሚሽን የውጪ ግብይቶች ከፍተኛ ባለሙያ ወይዘሮ መክሊት ፀጋዬ የቡና ልማትና ግብይት ላይ ያተኮረ ጥናታዊ ጽሑፍ ሲያቀርቡ እንደገለጹት፤ በ25 የኅብረት ሥራ ማኅበራት የቡና ወጪ ንግድ መጠን ላይ ጥናት ተደርጓል።

በጥናቱ መሠረት ማኅበራቱ የሚያቀርቡት የቡና የምርት መጠን ከሶስት ዓመት ወዲህ እየቀነሰ መጥቷል፤ የሚመለከታቸው አካላት የማኅበራቱን ወጪ ንግድ ለማሳደግ ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

በጥናቱም መሠረት ግለሰብ ላኪዎች በአነስተኛ ትርፍ ምርትን ወደ ውጭ በመላካቸው የማኅበራቱ ተሳትፎ ውስን እንዲሆን የራሱን አስተዋፅኦ ማበርከቱን ተናግረዋል።

በሌላ በኩል ለኅብረት ሥራ ማኅበራቱ የወጪ ንግድ ማነስ ቡና የአገር ውስጥ ዋጋው የተሻለ መሆኑ ሌላው ምክንያት መሆኑን ጠቁመው፤ በማኅበሩ አባላት በኩል በቂ ምርት ያለማቅረብና የዋጋ መዋዥቅ ችግሮች የማኅበራቱ የቡና ወጪ ንግድ መቀነስ ምክንያት መሆናቸውን ገልጸዋል።

በተጨማሪም የምርት መሰብሰቢያ ወቅታዊና በቂ ፋይናንስ አለማግኘት እንዲሁም አስተማማኝ የገበያ መዳረሻ አለማግኘት ማኅበራት መሰብሰብ ካለባቸው ምርት 65 በመቶውን ብቻ እንዲሰበስቡ ምክንያት መሆኑን አብራርተዋል፡፡

የኅብረት ስራ ማኅበራት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ አብዲ ዑመር በበኩላቸው በኅብረት ሥራ ማኅበራቱ የቡና ወጪ ንግድ ላይ ያለውን ችግር ነቅሶ በመለየት ባለድርሻ አካላት በሙሉ ዕቅዳቸው ውስጥ አካተው መፍትሔ እንዲገኝ የሚረዳ ሲምፖዚየሙ መዘጋጀቱን ተናግረዋል፡፡

በሲምፖዚየሙ ማኅበራት ያሉባቸውን ችግሮች እንዲያስረዱ አርሶአደሮችና ዩኒየኖች መሳተፋቸውን ጠቁመው፤ በተጨማሪ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የቡናና ሻይ ድርጅትን ጨምሮ ሌሎችም ባለድርሻ አካላት መሳተፋቸውን ገልጸዋል። ፡

ከሲምፖዚየሙ በኋላ የፖሊሲ፣ የአሠራርም ሆነ የአደረጃጀት ችግሮችን ከመፍታት በተጨማሪ የፋይናንስም ሆነ የገበያ ችግርን ለማቃለል በሚቻልበት መንገድ ላይ ውይይት እንደሚካሄድ አመላክተዋል፡፡

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ አክሊሉ ተገኝ በበኩላቸው፤ የኅብረት ሥራ ማኅበራቱ የወጪ ንግድ መቀነስ ምክንያቱ ውጫዊ ብቻ ሳይሆን በየማኅበራቱ ውስጣዊ ምክንያቶች ጭምር ሊፈጠር እንደሚችል ተናግረዋል።

የማኅበራት የፋይናንስ ችግር የምርት አቅርቦታቸው እንዲቀንስ ከፍተኛውን ሚና መጫወቱንም አስረድተዋል።

ከውጫዊ ችግሮች መካከል ደግሞ ግለሰብ ነጋዴዎች የቡና እሸትን በተሻለ ዋጋ ከአርሶአደር ላይ በመግዛት ምርቱን ለውጪ ገበያ እያቀረቡ በመሆኑ ማኅበራት ላይ ጉዳት እያስከተለ መሆኑን ገልጸዋል።

# አየር መንገዱ 36 ተጨማሪ አውሮፕላኖችን ሊያስመጣ ነው

**ፀጋዬ ጥላሁን**



አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ እያደገ ከመጣው የደንበኞች ፍላጎት ጋር ተያይዞ ተጨማሪ 36 አውሮፕላኖችን ለማስገባት ትዕዛዝ መስጠቱን አስታወቀ።

አየር መንገዱ የመጀመሪያው ቦይንግ 787 ድሪምላይነር አውሮፕላን በኢትዮጵያ አየር መንገድ ለመጀመሪያ ጊዜ በረራ የጀመረበት 10ኛ ዓመት አክብሯል። በበዓሉ የአየር መንገዱ የቦርድ ሰብሳቢ አቶ ግርማ ዋቄ፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን ጣሰው፣ የቦይንግ ኩባንያ ተወካዮች እና ሌሎች አካላት በተገኙበት ተከብሯል።

በወቅቱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን ጣሰው እንደገለፁት፤ አየር መንገዱ እያደገ ከመጣው የደንበኞች ፍላጎት ጋር ተያይዞ ሁለት ቦይንግ 787 ድሪምላይነር አውሮፕላንን ጨምሮ የተለያየ ሞዴል ያላቸውን ሠላሳ ስድስት ዘመናዊ አውሮፕላኖችን ለማስገባት ትዕዛዝ ሰጥቷል ብለዋል።

ሁለቱ 787 ድሪምላይነር አውሮፕላኖች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደሚገቡም ተጠቁሟል።

አየር መንገዱ 140 አውሮፕላኖች ውስጥም 27 አውሮፕላኖች ቦይንግ 787 ድሪምላይነር አውሮፕላኖች መሆናቸውን የጠቀሱት ዋና ሥራ አስፈፃሚው ተጨማሪ ሁለት አውሮፕላኖች በአንድ ዓመት ውስጥ ሲገቡ የቦይንግ 787 ድሪምላይነር አውሮፕላኖችን ቁጥር 29 ያደርሳል ነው ያሉት።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የቦይንግ 787 ድሪምላይነር አውሮፕላኑን ሲያስገባ ከአፍሪካ የመጀመሪያው፤ በዓለም ደግሞ ከጃፓን ቀጥሎ ሁለተኛ አየር መንገድ ነው። ይህም አየር መንገዱ ሁልጊዜም በአየር ትራንስፖርት ውስጥ በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከቀዳሚዎቹ አየር መንገዶች አንዱ መሆኑን ያሳያል ሲሉ አስረድተዋል።

እንደሳቸው ገለፃ፤ በአሁኑ ሰዓት አየር መንገዱ 130 መዳረሻዎች ያሉት ሲሆን የበረራ አውሮፕላኖች ቁጥርም ወደ 140 ደርሷል ነው ያሉት።

የቦይንግ ኩባንያ ተወካዮች በበኩላቸው፤ ድርጅቱ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር ያለውን ግንኙነት አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ተናግረዋል።

አየር መንገዱ የመጀመሪያውን ቦይንግ 787 ድሪምላይነር አውሮፕላን ነሐሴ 2012 ለመጀመሪያ ጊዜ ወደሀገራችን ማስገባቱ ይታወቃል።

# ኢትዮ ቴሌኮም "ኮንታክት ሴንተር" አገልግሎትን አስጀመረ

**ዘላለም ግዛው**



ፎቶ -አዩብ ተፈራ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ቴሌኮም የዲጂታል አገልግሎቶችን በማቅረብ ድርጅቶችና ተቋማት በዘመናዊ አሠራር ታግዘው ቀልጣፋና ተደራሽ የደንበኞች አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችላቸውን "የኮንታክት ሴንተር" ሥርዓት በተለያዩ አማራጮች አቀረበ።

ኢትዮ ቴሌኮም የአገልግሎቱን ማስጀመሪያ መርሐ ግብሩን ትናንት በሳይንስ ሙዚየም ባካሄደበት ወቅት፤ ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ ወይዘሪት ፍሬሕይወት ታምሩ የኮንታክት ሴንተር ሶሉሽን ሲስተም ኩባንያዎች በቀላሉ ከደንበኞች ጋር ለመገናኘት የሚያስችላቸው መሆኑን ተናግረዋል።

አገልግሎቱ ከዚህ ቀደም ደንበኞች በድምጽ እና በተለያዩ የሶሻል ሚዲያ በተናጠል ያስተናግዱ የነበሩትን የጥሪ ማዕከሎችን አሠራር ያዘመነ ነው ብለዋል።

በልዩ ልዩ አማራጮች ማለትም በድምጽ፣ በአጭር የጽሑፍ መልዕክት፣ በኢሜይል፣ በድረ ገጽ፣ በማኅበራዊ ሚዲያዎች እንዲሁም ቻት ቦትን ጭምር በመጠቀም የሚቀርቡ የደንበኞች ጥያቄዎችን በአንድ ላይ አቀናጅቶ ለኮንታክት ሴንተር ወኪሉ ማቅረብ የሚያስችል መሆኑንም ነው የገለጹት።

የቀረበው የቴክኖሎጂ አማራጭ የቢዝነስ ተቋማት ቀልጣፋና ተደራሽ አገልግሎት እንዲሰጡ፣ ወጪ ቆጣቢ የአሠራር ሥርዓት ለመከተል፣ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀጥሉ እና አዳዲስ አገልግሎቶችን ለመሸጥ የሚያስችላቸው መሆኑንም ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ ወይዘሪት ፍሬሕይወት ጠቁመዋል።

ኩባንያዎች ባላቸው የደንበኞች መጠን መግዛት የሚያስችላቸው፣ እንደአስፈላጊነቱም አቅሙን መጨመርና መቀነስ የሚያስችል ሲስተም እንደሆነም አመልክተዋል። አገልግሎቱ ኢትዮ ቴሌኮም ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማፋጠን ከሚተገብራቸው አገልግሎቶች መካከል እንደሚመደብም ተናግረዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ የኮንታክት ሴንተር ሶሉሽን የሚጠቀሙ ኩባንያዎች በተሠማሩበት ዘርፍ አገልግሎትን ማሳደግና የደንበኞችን ፍላጎት ማርካት ያስችላቸዋል። ልዩ ልዩ አማራጮች ይዞ በመቅረቡ ወደ ጥሪ ማዕከል ደውለው በመጠባበቅ የሚጠፋ ጊዜን ይከላከላል። ደንበኞች በማንኛውም ጊዜና ሰዓት በፈለጉት አማራጮች መስተናገድ ያስችላቸዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም የፋይናንስ ዘርፍ አካታችነትን በማረጋገጥ ላይ መሆኑን በመጠቆምም፤ የደንበኞቹን ቁጥር 68 ነጥብ 03 ሚሊዮን ማድረሱን፣ ደረጃውን በማሻሻል ከ781 የኦፕሬተር አቅራቢዎች መካከልም 23ኛ የኦፕሬተር አቅራቢ ደረጃ ላይ መሆን መቻሉንም አመልክተዋል። ድርጅቱ የሚሰጣቸው የቴሌብርና የፋይናንስ አገልግሎት ደንበኞች ሳይንገላቱ አገልግሎት እያገኙበት መሆኑንም አመልክተዋል።

ዜና

# ዓለምአቀፍ የኢንቨስትመንት ፎረም በአዲስ አበባ ሊካሄድ ነው

## - ፎረሙ በየዓመቱ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ገቢ ያስገኛል

**ሞገስ ጸጋዬ**




አዲስ አበባ፡- በየዓመቱ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ገቢ የማምጣት ዓላማ ያለው "ኢንቨስት ኦሪጅንስ" የተሰኘ ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ፎረም በአዲስ አበባ ሊካሄድ መሆኑን የፌዴራል መሬት ባንክና ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ።

የፌዴራል መሬት ባንክና ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሌንሳ መኮንን ፎረሙን አስመልክቶ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቁት፣ በየዓመቱ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ገቢ የማምጣት ዓላማ ያለው "ኢንቨስት ኦሪጅንስ" የተሰኘ ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ፎረም በጥር ወር 2015 ዓ.ም በአዲስ አበባ ይካሄዳል።

ከዚህም ሁለት ቢሊዮን ዶላር ገቢ መሰብሰብ አለብን ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ከአልሚዎች ጋር አምስት የመግባቢያ ሰነዶችን በመፈራረም ወደ ሥራ ለማስገባት ቅድመ ዝግጅት ላይ መሆናቸውንም ገልጸዋል።

ልማቶችን ለማልማት ስናስብ ዋናው አቅማችን የግል ባለሀብቱ ነው ያሉት ሥራ አስፈጻሚዋ፤ "ኢንቨስት ኦሪጅንስ" የተሰኘው ፎረም ኮርፖሬሽን ከተለያዩ የመንግሥትና የግል ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ልዩ ልዩ የኢንቨስትመንት አማራጮችን ወደ አገራችን ለመሳብ አስቦ የሚያዘጋጀው መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ገለጻ፤ ኮርፖሬሽኑ መሬቱን በማቅረብ ከባለሀብቶች ጋር በመሆን ወደ ልማት ይገባል። በዚህ ፎረም ኢትዮጵያ ያላትን ሀብት በማሳወቅ የተለያዩ የውጭ ባለሀብቶች ቤቶችንና የተለያዩ ድርጅቶችን እንዲገነቡ ይደረጋል። በተለይ በመኖሪያ ቤቶች፣ ጤና፣ ሆቴል፣ ትምህርትና አይሲቲ ዘርፎች ላይ የተለያዩ ጥራት ያላቸው ኢንቨስትመንቶች ወደ ኢትዮጵያ ገበያ እንዲሳቡ ለማድረግ ከፍተኛ ሥራ ይሠራል።

የሚዘጋጀው ፎረም ኮርፖሬሽኑ ካቀዳቸው በርካታ የኢንቨስትመንት እድሎችና ተግባራት መካከል የመጀመሪያው ነው ያሉት ሌንሳ መኮንን፣ ኮርፖሬሽኑ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ስትራቴጂ ቀርጾ ባለፉት ሁለት ዓመታት የተለያዩ ሥራዎች ሲሠራ ቆይቷል ብለዋል።

በዚህም በተለያዩ ሀገራት የሚዘጋጁ ፎረሞች ላይ በመሳተፍ ልምድና ተሞክሮ መወሰዱን ጠቁመው፤ በፎረሙ ላይ የሚሳተፉ ተቋማትና ባለሀብቶች በኮርፖሬሽኑ ስር ያሉ መሬቶችን ለማልማት የሚያስችሉ ስምምነቶችን በመፈራረምና መዋዕለ ነዋያቸውን እንዲያፈሱ በማድረግ ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ኢንቨስትመንት ለመሳብ ታቅዷል ሲሉም ተናግረዋል።

"ኢንቨስት ኦሪጅንስ" በሚል ርዕስ የሚዘጋጀው ፎረም በመሬትና ይዞታ ልማት ዘርፍ ኢትዮጵያን ከ5ቱ ዓለም አቀፍ ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻዎች ተርታ ለማሰለፍ ያለመ ነው።

ፎረሙ በሚካሄድበት ወቅት አልሚዎች በስፋት እንዲሳተፉና አቅም ያላቸውን ኢንቨስተሮችን ለመሳብ ስለ አሠራሩና ስላለው ሀብት ሰፋ ያለ ዝርዝር መረጃ እንደሚቀርብ ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ ገልጸዋል።

# የኢንቨስትመንት ዕድሎችን የሚያስተዋውቅ ኤክስፖ ሊካሄድ ነው

**ዳግማዊት ግርማ**




አዲስ አበባ፡- የኢንቨስትመንት ዕድሎችን የሚያስተዋውቅ 11ኛው የዶሮ ኤክስፖና ሰባተኛው የእንስሳት ሀብት አውደርዕይና ጉባኤ ከጥቅምት 17 እስከ 19 ቀን 2015 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ሊካሄድ መሆኑን አዘጋጆቹ አስታወቁ፡፡

በዓውደ ርዕዩ ላይ ከ10 ሀገራት ማለትም ከኢትዮጵያ፣ ከፈረንሳይ፣ ከጀርመን፣ ከሃንጋሪ፣ ከሕንድ፣ ከኬንያ፣ ከኔዘርላንድ፣ ከስኮትላንድ፣ ከቱርክ እና ከአሜሪካ የተውጣጡ ከ70 በላይ ኩባንያዎች ተሳታፊ ይሆናሉ ተብሏል፡፡

ሁነቱን የሚያስተባብረው የፐራና ኢቨንትስ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ነብዩ ለማ ትላንት በሰጡት መግለጫ እንዳሳወቁት፤ 11ኛው የዶሮ ኤክስፖ እና 7ኛው የእንስሳት ሀብት ዓውደ ርዕይ በወተት፣ በዶሮ እና የሥጋ እሴት ትስስር በመፍጠር፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በማስተዋወቅ፣ የእውቀት ሽግግርን በማምጣት የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ያስተዋውቃል፡፡

በኤክስፖው የዶሮና ወተት እሴት ሰንሰለትን ለመለወጥ ከፍተኛ የፖሊሲ ውይይት እና ስልጠና ይሰጣል፤ ያሉት አቶ ነብዩ፤ ኤክስፖው የግብርናን ምርታማነት በማሻሻል የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችል መሆኑንም ጠቁመዋል።

እነዚህ ተሳታፊዎች ከጠቅላላው የእሴት ሰንሰለቱ ውስጥ ሰፊውን ድርሻ የሚወክሉ ሲሆን ከመላው ኢትዮጵያ እና ከጎረቤት ሀገራት ከሚመጡ ከአራት ሺህ በላይ የዘርፉ የንግድ ባለድርሻ አካላት እና ባለሙያዎች ጋር የንግድ ግንኙነት ለመፍጠር መዘጋጀታቸውም ተጠቅሷል፡፡ በኤክስፖው ከ70 በላይ ዓለማቀፍ የዘርፉ መሪዎችና ቁልፍ የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የኢትዮጵያ ዶሮ አርቢዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ኤርሚያስ አለማየሁ በበኩላቸው እንደተናገሩት መሰል ፕሮግራሞች ዘርፉን እንዲሁም የዘርፉን ተዋንያን ያነቃቃል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በ10 ዓመት የልማት ዕቅዱ የወተት ምርትን ወደ 11 ነጥብ 8 ቢሊዮን ሊትር፣ የሥጋ ምርትን ወደ 1 ነጥብ 7 ሚሊዮን ቶን፣ እንቁላል 5 ነጥብ 5 ቢሊዮን እንዲሁም የዶሮ ሥጋ ምርትን 106 ሺህ ቶን ለማድረስ አቅዷል። ይህም የእንስሳት ተዋፅዖ ምርቶች የነፍስ ወከፍ ፍጆታን በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል።

በ2012 ዓ.ም. የዶሮ እርባታ ዘርፍ 88 ሺህ 572 ዶላር የሚያወጣ 35 ቶን የዶሮ ምርት ወደ ሶማሊያ ቢልክም፣ ሀገሪቱ አሁንም የተጣራ የዶሮ ምርቶችን አስመጪ ነች።

ፐራና ኢቨንትስ በኢትዮጵያ ውስጥ ዘርፈ ብዙ የንግድ ትርዒት እና የቢዝነስ ኩነቶች በማዘጋጀት እና በማማከር ሥራ ላይ የተሠማራ እና ዘርፉን በእውቀት በቴክኖሎጂ እና በግብዓቶች ለመደገፍ ዓላማ አድርጎ የተቋቋመ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ነው፡፡



አቶ ጣሂር መሐመድ

# የጣና ፎረም ተጨማሪ የቱሪዝም እድል ሆኗል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የጣና ፎረም ከውይይቱ ጎን ለጎን ተጨማሪ የቱሪዝም እድል በመሆን ትልቅ አሻራን ጥሎ አልፏል ሲል የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ።

የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አቶ ጣሂር መሐመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ሰሞኑን በደኅንነት ጉዳዮች ላይ አተኩሮ በባህርዳር ከተማ የተካሄደው አስረኛው የጣና ፎረም ከጉባዔነት ባሻገር በአካባቢው ያለውን የኮንፈረንስ ቱሪዝም በማሳደግ ላይ ትልቅ አሻራ ጥሎ አልፏል። ከሀይማኖታዊና ታሪካዊ ሁነቶች ባሻገር ለኮንፈረንሶች ልዩ ትኩረት በመስጠት ቱሪዝሙን ማሳደግ እንደሚቻል ተሞክሮ ተወስዶበታል።

በስብሰባ ምክንያት ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ የሚኖር እንቅስቃሴ የኮንፈረንስ ቱሪዝም ላይ በጎ ተጽዕኖ እንዳለው የጠቀሱት አቶ ጣሂር፤ ጉባዔው ከፎረምነት ባሻገር በአካባቢው ያለውን የኮንፈረንስ ቱሪዝም ማሳደግ ላይ ትልቅ አሻራ ጥሎ ማለፉን አስታውቀዋል።

እንደ አቶ ጣሂር ገለጻ፤ ፎረሙ እንደ ክልል ባህር ዳር ከተማ ላይ እንደመካሄዱ በርካታ እንግዶች ተገኝተዋል። ከፎረሙ መካሄድ አስቀድሞ እንግዶች የቱሪስት መዳረሻዎችን እንዲጎበኙ የማመቻቸት ቅድመ ዝግጅት ተደርጎ ነበር። በእንግዳ አቀባበል ዙሪያ ምን መሠራት አለበት ተብሎ በተለየው መሠረት በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል። በዚህም የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤትንና የሚመለከታቸው አካላትን ጨምሮ፤ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲሁም ፎረሙን ከሚያዘጋጀው ሴክሬቴሪያት ጋር የጸጥታ፣ የመስተንግዶና አቀባበል ሥራዎች ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በትብብር ተሠርተዋል።

ፎረሙ ከጀምረበት ጊዜ አንስቶ እንግዶችን በመቀበል የማስተናገድ ሥራው ውጤታማ እንደነበር በመጥቀስ፤ ከኤርፖርት ጀምሮ ባለው የእንግዶች አቀባበል የሀገርን ባህል ሊያስተዋውቁ የሚችሉ ትዕይንቶች እንደነበሩ ገልጸዋል። ባህልንና በአካባቢው የቱሪስት መስህብ የሆኑ ሥፍራዎችን የማስጎብኘት ሥራዎች መከናወናቸውንም ተናግረዋል።

በፎረሙ ማጠናቀቂያም የሀገራት መሪዎች ጭምር በቅርበት የሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎችን መጎብኘታቸውንና በዚህም ደስተኞች እንደነበሩ አቶ ጣሂር ገልጸዋል። ይህም ተጨማሪ የቱሪዝም እድል በመሆን ትልቅ አሻራን ጥሎ አልፏል ነው ያሉት።

እንዲህ አይነት ሁነት በአካባቢው ከትናንሽ የንግድ ሥራዎች እስከ ትልልቅ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ያሉትን ተጠቃሚ የሚያደርግ እንደሆነ ጠቁመዋል። ይህ ለኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ተጨማሪ ግብዓት እንደሆነም አመላክተዋል። በቱሪዝሙ መስክም ባህልን የማስተዋወቅና የቱሪዝም መስኩን በተሻለ ሁኔታ ለማሳደግ ትልቅ ተሞክሮ እንደተወሰደበት ገልጸዋል።

ፎረሙ ጣና ላይ እንደመካሄዱ በርካታ የቱሪዝም መስህቦችን ለመጎብኘት እድል እንዳለውና ጣና ፎረምን ጨምሮ በሚቀጥለው ዓመት ከውይይቱ ጎን ለጎን የቱሪዝም እንቅስቃሴውን ለማስፋት ሰፊ እቅድ መያዙን አቶ ጣሂር አስታውቀዋል። ይህንን በተመለከተ እስከ መጪው ሰኔ ወር ድረስ ስትራቴጂ ተሰርቶ እንደሚጠናቀቅም ጠቁመዋል።

አቶ ጣሂር እንዳሉት፤ በዓላትን ከመጠበቅ ባሻገር ተሰብሳቢዎች የበዓላትን ዐውድ ሳይጠብቁ ሲምፖዚየም፣ ፓናል፣ ኮንሰርቶችንና መሰል ሁነቶችን አስታኮ ቱሪዝሙን ለማነቃቃት ስምምነት ተፈጥሮ እየተሠራ ነው። ይህም ዘርፉን የበለጠ ያጠናክራል። ይህ ባህርዳር ብቻ ሳይሆን እንደ ደሴና ደብረ ማርቆስ ባሉ ከተሞች ጭምር ተፈጻሚ ይሆናል።

# በሰሜን ኢትዮጵያ በተፈጠረው ግጭት ከቁጥጥር ውጪ የወጣ ነገር አለመኖሩን አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ገለጹ



**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በሰሜን ኢትዮጵያ በተፈጠረው ግጭት ከቁጥጥር ውጪ የወጣ ነገር እንደሌለና ሁሉም ነገር በታቀደው መሠረት እየሄደ መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ሚኒስትር አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ገለጹ፡፡

አምባሳደር ሬድዋን ትናንት በትዊተር ገጻቸው ላይ ባሰፈሩት መልዕክት እንደገለጹት፤ መንግስት የአፍሪካ ኅብረት የሰላም ውይይቱ የሚካሄድበትን ቀን እስኪያሳውቅ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል።

"አንዳንዶች በሰሜን ኢትዮጵያ የተፈጠረው ግጭት ከቁጥጥር ውጪ ሆኗል በሚል እየተጠቀሙበት ያለው አገላለጽ ከእውነት የራቀ ነው" ያሉት አምባሳደር ሬድዋን፤ "ግጭቱ ወደ አማራና አፋር ክልሎች ተስፋፍቶ ነበር፤ አሁን ያ ነገር የለም፤ የመከላከል እርምጃው በታሰበው መልኩ እየሄደ ይገኛል" ብለዋል፡፡

የሰብዓዊ እርዳታ አቅርቦትና አገልግሎትን እንደሚጀመርም አምባሳደር ሬድዋን ገልጸዋል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ ትናንት በሰጡት መግለጫ "በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ከቁጥጥር ውጪ እየሆነ ነው" በሚል ከእውነታ የራቀ አስተያየት መስጠታቸውንም አምባሳደር ሬድዋን ጠቅሰዋል።

የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ትናንት ባወጣው መግለጫ መንግሥት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ለማስከበር በትግራይ ክልል የሚገኙ የአውሮፕላን ማረፊያዎችን፣ የፌዴራል ተቋማትንና ታላላቅ መሠረተ ልማቶችን ለመጠበቅ እንደሚገደድ መግለጹ ይታወሳል።

## "የውጭ ምንዛሪ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እገዳ እንዲጣልባቸው ከተዘረዘሩት ሚዛን የሚደፉት ተሽከርካሪ እና ከተሽከርካሪ ጋር የተያያዙት መሆናቸውን የጠቆሙት አቶ ክቡር ገና፤ እነዚህ ቀርተው ገንዘቡን ለመሠረታዊ የፍጆታ እቃዎች እና ለልማት እንዲውል ማድረጉ ጥሩ ርምጃ መሆኑን ተናግረዋል።

ብሔራዊ ባንክ ከውጭ ይገቡ በነበሩ ምርቶች ላይ የጣለው እገዳ እንደአጋጣሚ የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ባለመሆናችን ብዙም አንቸገርም ያሉት አቶ ክቡር፤ አባል ብንሆን ኖሮ አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል።

አቶ ክቡር እንዳሉት፤ ብሔራዊ ባንክ ከበፊቱም በጥቁር ገበያ ላይ የሚደረጉትን ግብይቶች አልፈቀደም። አሁንም የተወሰዱት ርምጃዎች ያንን ለማጠንከር የተወሰነ ነው። ድርጊቱን የሚፈጽሙት ሕገ ወጦች ነበሩ፤ አሁንም ሕገወጥ ናቸው፤ ነገር ግን መንግሥት ለጉዳዩ ትኩረት መስጠቱ መልካም ነው ሲሉም ተናግረዋል።

ውሳኔውን ተከትሎም በጥቁር ገበያ በሚደረገው ግብይት የአንድ ዶላር ዋጋ ከ100 ብር በላይ ደርሶ የነበረውን በመጀመሪያዎቹ ጊዜያት በማስተካከል ፖሊሲው ውጤት እያመጣ መሆኑን ያሳያል። ይህ እስከመቼ ይቀጥላል የሚለው ገና አልታወቀም። የመጀመሪያዎቹ ምልክቶች ግን የተፈለገውን ዓላማ ለማሳካት እንደሚያስችል አሳይቷል ብለዋል።

በቂ ምርቶች በብቃት አለመግባታቸው ወይም አለመመረታቸው ግሽበትን እንዲፈጠር ማድረጉንም በመጠቆም፤ በሰዎች እጅ ብዙ ገንዘብ አለ፤ ነገር ግን ሰው የሚፈልገውን የሚያገኝበት ሁኔታ አልተፈጠረም ሲሉም አክለዋል።

በአጠቃላይ ሲታይ ትልቁ ግሽበት እየመጣ ያለው በምግብ በመሆኑ በተለይ አቅመ ደካማውን የሚጎዳ ነው። ከተማ ውስጥ የሚታየው የቤት ኪራይና ሽያጭ ላይ የሚስተዋለው ዋጋ ከዕለት ወደ ዕለት እየናረ ሄዷል። አንዳንድ ሀገራት ከተወሰነ ገንዘብ በላይ የሚያወጣ ሽያጭ ካለ ታክሱ በጣም ከፍተኛ ይሆናል። በእኛ ሀገርም መጠናት ይኖርበታል ብለዋል።

አሁን የተወሰደው ርምጃ በተወሰነ መልኩ የውጭ ምንዛሪ ቢያድንም ምን ያህል? የሚለው ጥያቄ ውስጥ ሊገባ ይገባዋል። ምክንያቱም እገዳ የተጣለባቸው ከአውቶሞቢል ውጭ ሌላው ቢተመን በዓመት ውስጥ ከ100 ሚሊዮን ዶላር በታች እንጂ ከእዛ በላይ አያወጣም። በርግጥ ይሄ ቀላል ነው ማለት ባይሆንም ሚዛን ደፊ አይደለም ብለዋል።

ሂደት የሚጠይቅ ቢሆንም ምርት ማሳደግ ላይ መሥራት ያስፈልጋል ያሉት አቶ ክቡር፤ አስፈላጊ ናቸው የሚባሉ ድርጅቶች ካሉ ግብዓቶችን በቀላሉ እንዲያገኙ፣ የገንዘብም ሆነ የብድር ድጋፍ ቢመቻች በአጭር ጊዜ ውስጥ ምርቱን አሳድገው የገበያውን ዋጋ ሊያስተካክሉት ይችላሉ ሲሉም ተናግረዋል።

በዋናነት ግን በተለይ የግብርና ምርትን ማሳደግ ላይ ብዙ ሊሠራ ይገባል። በአገር ውስጥ ያለው ሃብት መሬት እንደመሆኑ ምርትን ማሳደግ በሚቻልበት መንገድ ጥቅም ላይ በማዋል መሠረታዊ ችግሩን መፍታት ያስፈልጋል ሲሉም ምክረ ሃሳባቸውን ለግሰዋል።

## መንግሥት በትግራይ ሰብዓዊ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የመከላከያ ሠራዊት በከተሞች ጦርነት እንዳይደረግ የተከተለው ጥብቅ ዲሲፕሊን ንጹሐን እንዳይጎዱ ማድረጉን ያነሳው መግለጫው፤ ሠራዊቱ አሁን ላይ ሽሬ፣ አላማጣ እና ኮረም ከተሞችን ያለ ከተማ ውጊያ መቆጣጠር መቻሉን አስታውቋል።

ይህ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የተከተለው ጥብቅ ወታደራዊ ዲሲፕሊን፣ የአሸባሪው ሕወሓትን ፕሮፖጋንዳ ሲያስተጋቡ የነበሩ አካላትን ሚርት ያመከነ ነው ሲልም በመግለጫው ተመላክቷል።

ከልዩ ልዩ የርዳታ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት፣ መከላከያ በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች ርዳታ በተሳለጠ መንገድ እንዲደርስ የኢትዮጵያ መንግሥት በቂ ዝግጅት ማድረጉን መንግሥት ገልጿል።

የሰብዓዊ ርዳታ አቅርቦቱ የሽሬ አውሮፕላን ማረፊያን ተጠቅሞ ርዳታ ማድረስን እንደሚጨምር አገልግሎቱ በመግለጫው አስታውቋል።

መንግሥት ከሰብዓዊ የርዳታ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ሰብዓዊ ርዳታ የሚደርስባቸውን መንገዶች እያስፋፋ መሆኑን የጠቆመው መግለጫው፤ በተቀናጀ መንገድ በሰሜን ጎንደር በኩል ወደ ሽሬ የሚወስደውን እና ከኮምቦልቻ- ደሴ- ወልድያ- ቆቦ- አላማጣ የሚወስደውን መንገድ ለሰብዓዊ ርዳታ ሥራ ለማዋል እየሠራ መሆኑን ገልጿል።

ይሄንን የሰብዓዊ ርዳታ ሥራ የሚያሳልጥ ኮሚቴ ከሚመለከታቸው አካላት ተወጣጥቶ ሥራ መጀመሩን አገልግሎቱ አስታውቋል።

ሥራዎቹ ቴክኒካዊ የሆኑ ጥናቶችን እና ግጭት በነበረባቸው አካባቢዎች አገልግሎቶችን ለማስጀመር የሚያስችሉ መሠረታዊ ሥራዎችን እንደሚጨምር የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ያወጣው መግለጫ አመላክቷል።

## ሀገራዊ ምክክሩን አካታች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኃላፊነት ለመወጣት ከፍተኛ ዝግጅት እያደረገ ሲሆን እስካሁን ባለው ሂደትም በቅድመ ዝግጅትና የዝግጅት ምዕራፍ ምክክሩን አካታች ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል:: በዚህም መሠረት ኮሚሽኑ ሁሉንም አካላት እና የኅብረተሰብ ክፍሎች አካታች ለማድረግ በሩ ክፍት መሆኑን ገልጸዋል::

ኮሚሽኑ እስከ አሁን የሠራው የሦስት ዓመት እቅድ ዝግጅትና በባለሙያ ማስገምገም፣ የ2015 ዓ.ም ሥራ መርሐ ግብር ዝግጅት፣ የበጀት ዝግጅት፣ ውጪ ሀገር ከሚገኙ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ለማጠናከር የሚያስችሉ ሥራዎችን ጨምሮ የሁለተኛ ምዕራፍ ዝግጅት ሥራዎችን ለማገባደድ በሂደት ላይ ነው::

ኮሚሽኑ ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎችን ማስቀመጡን የጠቆሙት ፕሮፌሰር መስፍን በዚህም መሠረት ወረዳዎችን የሚመሩ አመራሮችና ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶችን እና መሐል ያለውን አመራር የሚመሩ ዘርፎች፣ የታሳታፊዎች ልየታ፤ አጀንዳ መረጣና ቀረጻ የሚያካሂዱ ዘርፎች እንዲሁም ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያስችሉ ሥልጠናዎችን ለማካሄድ እና በሚዲያና ኮሙኒኬሽን ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ ዘርፎችን የማደራጀት ሥራ መከናወኑን ጠቁመዋል::

የውይይት ጽንሰ ሃሳቦች እና ሂደቶች ኅብረተሰቡ ጋር እንዲደርሱ ለማድረግ በተለያዩ ቋንቋዎች የሚዲያ ተደራሽነት ወሳኝ በመሆኑ ዘርፉ ይህንን ለማከናወን ሥራውን በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል ብለዋል::

ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ፣ከአፋር፣ ከጋምቤላ እና ከአዲስ አበባ የተውጣጡ የዞንና ወረዳ ኃላፊዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች ፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች እስከ አሁን ድረስ የተሠሩ የኮሚሽኑን ሥራዎች እንዲገመግሙ ተደርጓል ያሉት ፕሮፌሰር መስፍን፣ በቀጣይ አስር ቀናት ውስጥ በቀሩት ክልሎች የኮሚሽኑን ሥራ የማስገምገም ሥራ ይቀጥላል ብለዋል::

እንደ ፕሮፌሰር መስፍን ገለጻ፤ ሁሉም የኅብረተሰቡ ክፍሎች በተወካዮቻቸው አማካይነት እንዲሳተፉ ለማድረግ የተሳታፊዎች ልየታ ማካሄድ አስፈላጊ ነው:: ይህን እውን ለማድረግ ባለድርሻ አካላት በአጀንዳ ቀረጻ ላይ እንዲሳተፉ ከ1 ሺህ 300 ወረዳዎች የተውጣጡ ተወካዮች እንዲካተቱ ለማድረግ እየተሠራ ነው ::

ክብርት የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳሕለወርቅ ዘውዴ በዘንድሮው የሕዝብ እና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች የጋራ ስብሰባ መክፈቻ ንግግራቸው ከገለጹት ውስጥ ትልቁ የትኩረት አቅጣጫ ለኮሚሽኑ የተሰጠውን ተልዕኮ እንዲሳካ ድጋፍ ማድረግ መሆኑን እንደጠቀሱ የተናገሩት ፕሮፌሰር መስፍን፣ ይህንንም ተከትሎ ኮሚሽኑ ለክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች ፣ ለክልሎች ምክር ቤት አፈ ጉባዔዎች፣ ለፓርላማ ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ለፌዴሬሽን እና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች አፈጉባዔዎች በኮሚሽኑ ሥራ ዙሪያ ሰፊ ገለጻ ተደርጎላቸዋል ብለዋል::

ከኢትዮጵያ ውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ለማግኘትም ከዲያስፖራ አገልግሎት ጋር በመሆን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል::

ኮሚሽኑ ሁሉንም ምዕራፍ ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ በጥንቃቄ እየሄደበት ይገኛል ያሉት ፕሮፌሰር መስፍን፣ ችኮላ ፣ የመንግሥት እና የውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት የምክክር ሂደቱን ስለሚያደናቅፍ ይህ እንዳይሆን ጥንቃቄ ተደርጎ እየተሠራ ነው ብለዋል::

መፍትሔ የሚያመጡ አጀንዳ የሚሰበሰበው ከሕዝብ በመሆኑ ሰብስቦ ለመጨረስ ምን ያክል ጊዜ እንደሚጠይቅ ስለማይታወቅ የትግበራ ቀን ቆርጦ ማስቀመጥ አዳጋች እንደሆነም ጠቁመዋል::

ግጭት ባለባቸው አካባቢዎችንም በምክክሩ አካታች ለማድረግ ኮሚሽኑ ለሁሉም በሩን ክፍት አድርጎ እየሠራ ነው ያሉት ፕሮፌሰር መስፍን፣ ለዚህም በተደጋጋሚ ጥሪ ማቅረባቸውን ጠቁመዋል:: በመሆኑም ምክክሩ ሁሉንም አካታች እንዲያደርግ ሁሉም ድጋፍ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል ::

## የሰላም ውይይቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በአንድ ሀገር ውስጥ ሁለት የታጠቁ ኃይሎች ሊኖሩ እንደማይችሉ ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች እንደሚከለክሉ ጠቅሰው፤ በአፍሪካ ኅብረት መሪነት በአሸባሪው ሕወሓት እና በመንግሥት መካከል የሚደረገው የሰላም ውይይት ስኬታማ እንዲሆን ካስፈለገ ሕወሓት ትጥቅ ፈትቶ ለመነጋገር ዝግጁ መሆን እንደሚኖርበት ገልፀዋል፡፡

በየትኛውም ሕግ ይሁን ድንጋጌ በአንድ ሀገር ውስጥ ሁለት የታጠቀ ኃይል ሊኖር አይችልም ያሉት የፖለቲካና ዓለም አቀፍ ምሑሩ፤ በመሆኑም አሸባሪው ሕወሓት ትጥቁን ካልፈታ ሰላም ሊኖር እንደማይችል መታወቅ አለበት ሲሉ አፅንዖት ሰጥተው ተናግረዋል፡፡

በሌሎች ሀገራት በተፈጠሩ ተመሳሳይ ክስተቶች አማፂዎች ለሰላማዊ ንግግር ሊቀርቡ የሚችሉት ትጥቅ ፈትተው እንደሆነ የጠቆሙት አቶ ሱራፌል፤ አሸባሪው ሕወሓት ለሰላም ንግግሩ መሣሪያውን ታጥቆ የሚቀርብ ከሆነ በአፍሪካ ቀንድም ሆነ በኢትዮጵያ ሰላም ሊገኝ አይችልም ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በተመሳሳይ የሰላም ድርድሩ በስኬት እንዲቋጭ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አሸባሪው ሕወሓት ትጥቅ እንዲፈታ ግፊት ሊያደርግ እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

አቶ ሱራፌል፣ የሰላም ውይይቱ በስኬታማነት እንዲቋጭ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ሕወሓትን እሽሩሩ ማለት አቁሞ የሰላም ሂደቱን እንዲቀበል እና ጦርነት እንዲያቆም ከፍተኛ ግፊት ማድረግ አለበት ሲሉም መክረዋል፡፡

በሌላ በኩል መንግሥት፣ ዓለም አቀፉን የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ በመሰብሰብ ከዚህ በፊት ሲደረጉ ስለነበሩ ነገሮች ግልፅ በሆነ መንገድ ማሳወቅ ይኖርበታል ያሉት አቶ ሱራፌል፤ እነዚህ የሀገራት ዲፕሎማቶች ሕወሓት ለሰላም ድርድሩ ትጥቁን እንዲፈታ እና ለሰላም ድርድሩ ዝግጅት እንዲያደርግ ግፊት እንዲያደርጉ ማድረግ እንደሚኖርበትም ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት የትግራይ ክልልን ሙሉ ለሙሉ ሊቆጣጠር እንደሚገባ እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶችም ሆነ ምዕራባውያን መንግሥታት ፌዴራል መንግሥትንና አሸባሪውን ሕወሓትን እኩል ማየታቸውን ማቆም እንደሚኖርባቸውም ጠቅሰዋል፡፡

ምዕራባውያን ሚዲያዎችም ሆነ መንግሥታት አሸባሪውን ሕወሓት እና የኢትዮጵያን መንግሥት እኩል የማየት አዝማሚያ እንደሚስተዋልባቸው ገልፀው፤ ይህ ግን ትክክል እንዳልሆነ ተናግረዋል፡፡ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶችም በዚህ ላይ ጠንከር ያለ ሥራ መሠራት ይኖርበታል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

በተለይ በምዕራቡ ዓለም ያሉ ዲፕሎማቶች አሸባሪው ሕወሓት ድጋፍ እንዳያገኝ የሚያደርጉ ሥራዎችን እና አሸባሪነቱ ተለይቶ እንዲታወቅ የሚያስችሉ ሥራዎችን መሥራት ይኖርባቸዋል ሲሉም አክለዋል፡፡

## የ12ኛ ክፍል የተፈጥሮ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደሚገኙ መመልከታቸውን የገለጹ ሲሆን በመጀመሪያው ዙር የታዩ ድክመቶችን በማሻሻል ለሁለተኛው ዙር የተሻለ ዝግጅት በመደረጉ እስካሁን ያጋጠመ ችግር አለመኖሩን ጠቁመዋል፡፡

ዘንድሮ በተለየ ቦታና የፈተና ሂደት በዩኒቨርሲቲዎች እየተሰጠ ያለው የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና በተሳካ መልኩ እየተከናወነ ሲሆን በሁለተኛው ዙር የፈተና አሰጣጥ መርሐ ግብር በ130 የፈተና ጣቢያዎች በሙሉ ፈተና መጀመሩን ፕሮፌሰር ብርሃኑ ተናግረዋል፡፡

ፈተና ከሚሰጥባቸው ዩኒቨርስቲዎች አንዱ በሆነው በአዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ ያለውን የፈተና ሂደት በተመለከተ ኢዜአ እንደዘገበው፤ በዩኒቨርስቲው በሁለተኛ ዙር ለተፈጥሮ ሳይንስ የ12ተኛ ክፍል ተማሪዎች ፈተናው በመሰጠት ላይ ነው፡፡

በዩኒቨርሲቲው 4 ሺህ 851 የተፈጥሮ ሳይንስ ተፈታኞች ለፈተናው መቅረባቸው የተገለፀ ሲሆን ተማሪዎቹ ሰኞ እለት ስለፈተናው ገለፃ እንደተደረገላቸውና በጊቢው ውስጥ ማግኘት የሚገባቸውን አገልግሎቶች እያገኙ መሆኑንም ተመልክቷል።

በተመሳሳይም የመዳወላቡ ዩኒቨርሲቲ የተመደቡለትን ከ4 ሺህ የሚበልጡ የ12ኛ ክፍል የተፈጥሮ ሳይንስ ተፈታኞች እያስፈተነ መሆኑን አስታውቋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶክተር አህመድ ከሊል በመጀመሪያው ዙር የማኅበራዊ ሳይንስ ፈተና 11 ሺህ ተማሪዎችን ዩኒቨርሲቲው ተቀብሎ ያለምንም ችግር ማስፈተኑን ተናግረዋል።

ለተፈጥሮ ሳይንስ ፈተናም በመጀመሪያ ዙር የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን በማዳበርና ክፍተቶችን በመቅረፍ 4 ሺህ 412 ተፈታኞችን መፈተን የሚያስችል ዝግጅት በማድረግ ማስፈተን ጀምሯል ብለዋል።

ዶክተር አሕመድ እንዳሉት በአንደኛው ዙር በዩኒቨርሲቲው የተመደቡ ተፈታኞች ያሳዩት መልካም ስነምግባር አሁንም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ስለፈተናው አጠቃላይ ገለጻ ተደርጓል።

ፈተናውን የሚወስዱ ተማሪዎችም ከሚናፈሱ የሐሰት መረጃዎች መራቅና ትኩረታቸውን ፈተናው ላይ ብቻ በማድረግ የተሻለ ነጥብ እንዲያስመዘግቡ መክረዋል።

በዩኒቨርሲቲው በተደረገላቸው ገለጻ ለፈተናው መዘጋጀታቸውን ተፈታኞች ገልጸዋል።"ፈተናው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ እንዲሰጥ መደረጉ ሌብነትን በማስቀረት ሁሉም የላቡን እንዲያገኝ እድል ስለሚፈጥር ደስተኛ ነን" ሲሉ ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሉዓላዊነትን እያስከበሩ ለሰላም ሳይታክቱ መሥራቱ ሕጋዊም ተገቢም ነው!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሉዓላዊነቱ ቀናኢ ነው፡፡ በዚህም በየዘመናቱ ከውስጥና ከውጭ የተቃጡ ሉዓላዊነትንና የግዛት አንድነትን የሚፈታተኑ ተግባራትን በጽኑ ታግሎ ኢትዮጵያን ከነሙሉ ክብሯ ለአሁኑ ትውልድ አስረክቧል፡፡ የአሁኑ ትውልድም የአባቶቹን አደራ በመረከብ የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በደሙና በአጥንቱ በማስከበር ላይ ይገኛል፡፡

ከጥንት እስከ ዛሬ የቅርብ እና የሩቅ ጠላቶች ከሀገር ውስጥ ባንዳ አሸባሪዎች ጋር ተባብረው ኢትዮጵያን ለመበታተን መሄድ እስከሚችሉት ድረስ ተጉዘዋል፡፡ ለዘመናት አብሮ የኖረው ሕዝብን በብሔርና በሃይማኖት በመከፋፈል እርስ በእራሱ እንዳይተማመንና በሂደትም በሚኖሩ ግጭቶች ኢትዮጵያ እየተዳከመች እንድትሄድ ያለማሰለስ ሠርተዋል፡፡ ለሀገሪቱ መዳከምና በሂደትም መፈራረስ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚሉትን ኃይል በማደራጀት፤ በማስታጠቅና በማሰልጠን ታሪካዊ ጠላትነታቸውን በገሃድ ሲያስመሰክሩ ኖረዋል፡፡ አሸባሪውን ትሕነግን የመሳሰሉ የሸብር ኃይሎችን የልብ ልብ ሰጥተው፤ አቅፈውና ደግፈው ለስልጣን በማብቃት ኢትዮጵያ በጊዜ ሂደት እንድትዳከምና ብሎም እንድትፈራርስ በረኸሙ አልመው ሠርተዋል፡፡

በዚህ ሂደት የመጣው የሸብር ኃይሉ ትሕነግም በገዛ ሀገሩ ላይ ጠላት ሆኖ ኖሯል፡፡ ከጌቶቹ የተሰጠውን ኢትዮጵያን የማፈራረስና ብሎም በኢትዮጵያ ፍርስራሽ ላይ የራሱን ኢምፓየር የመገንባት ሕልም አንግቦ ለ27 ዓመታት ያህል ሀገሪቱን በጭቆናና በግፍ ሲገዛ ቆይቷል፡፡ ለኢትዮጵያ አንድነት ምሶሶ የሆኑ ብሔሮችን በማይጨበጥ ስሜት በማነሳሳትና የጥላቻ ትርክትን በማስፋፋት የሀገሪቱ ሕልውና እንዲናጋ በብዙ ሠርቷል፡፡ በየቦታው በሚሸርባቸው እኩይ ሴራዎችም ኢትዮጵያውያን በጥርጣሬ እንዲተያዩና በአንድነት እንዳይቆሙ የጥላቻ ሐውልት ሲያቆምም ኖሯል፡፡

አሸባሪ ትሕነግ በስልጣን ላይ እያለ ጭምር የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ለውጭ ባዕዳን አሳልፎ በመስጠት ይታወቃል፡፡ ከዚህ በከፋ መልኩም « ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ከካርታ ላይ መፋቅ አለባት»፤ «እኛ የሚያስደስተን ኢትዮጵያ ስትፈራርስ ማየት ነው»፤«ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሲያልም ቢሆን እወርዳለሁ» የሚሉ ፀረ ኢትዮጵያ አቋሞችን ያለ ሀፍረት በማራመድ ማንነቱን ገልጿል፡፡ ይህንኑ ውጥን ከዳር ለማድረስም የሰሜን ዕዝን ከጀርባው ከመውጋት ጀምሮ ከአንድም ሦስት ጊዜ ጦርነት በመክፈት ኢትዮጵያ በሂደት እንድትዳከምና ብሎም በሂደት እንድትፈራርስ አልሞ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

ነሐሴ 18 ቀን 2014 ዓ.ም አሸባሪው ትሕነግ ሦስተኛውን ዙር ጦርነት የከፈተው የኢትዮጵያ መንግሥት በአፍሪካ ኅብረት በኩል በሚደረገው የሰላም ንግግር፣ ያለ ቅድመ ሁኔታ በየትኛውም ጊዜና ቦታና ጊዜ ላይ ለመነጋገር ዝግጅነቱን ከገለጸ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ነው። አሸባሪው ትሕነግ በሙሉ አቅሙ ጥቃት ከመክፈቱ በፊት የኢትዮጵያን የአየር ክልል ደጋፊዎቹ በሆኑ የኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች ሲያስደፍር ቆይቷል። በዚህም የተነሣ የኢትዮጵያ መንግሥት የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት የመጠበቅ ግዴታውን እንዲወጣ አስገድዶታል።

የኢትዮጵያ መንግሥት የሚወስዳቸው ርምጃዎች የግድ አስፈላጊ የሆኑት በአሸባሪው ትሕነግ ተደጋጋሚ ጥቃት የተነሣ ብቻ ሳይሆን ከሀገሪቱ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር ተቀናጅቶ በሚፈጽማቸው ተግባራት ምክንያት ጭምር ነው። ስለሆነም የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ለማስከበር የኢትዮጵያ መንግሥት የአውሮፕላን ማረፊያዎችን፣ የፌዴራል ተቋማትንና ታላላቅ መሠረተ ልማቶችን የግድ መጠበቅ ይኖርበታል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ሉዓላዊነትንና የግዛት አንድነትን ለማስጠበቅ የሚያከናውናቸው ተግባራት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት ፡፡ አንደኛው የሸብር ቡድኑ ባነገሰው ጦርነትና የጥላቻ ፖለቲካ ዛሬ የትግራይ ሕዝብ ለበርካታ ቀውሶች ተዳርጓል፡፡ የኤሌክትሪክ አገልግሎት፤ ውሃ፤ የስልክ፤ የባንክ እና የትምህርት አገልግሎቶችን ማግኘት አልቻለም፡፡ በየጊዜው ለሰብዓዊ ርዳታ የሚገባውንም እህል ላደራጀው ታጣቂ ቡድን በማከፋፈል ሕዝቡን በማስራብ ላይ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ የትህነግ የሽብር ቡድን በትግራይ ሕዝብ ላይ ተነግሮ የማያልቅ ግፍና በደልም በመፈጸም ላይ ይገኛል፡፡ ስለዚህም ኢትዮጵያዊ የሆነውን የትግራይ ሕዝብ ከዚህ ክፉ ቡድን መንጋጋ ማላቀቅ የኢትዮጵያ መንግሥት አንዱ ግዴታ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሰብዓዊ ርዳታን ለተረጂዎች በተገቢው ሁኔታ እንዲያሳልፍ የሚረዳው ይሆናል።

በአጠቃላይ በዚህ ወሳኝ ወቅት የኢትዮጵያ መንግሥት ሁለት ዓቢይ ጉዳዮችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በአንድ በኩል የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና ግዛት አንድነት ማስጠበቅ በሌላ በኩል ደግሞ በየትኛውም ጉዳይ ላይ ፤ በማንኛውም ጊዜና ቦታ ለመነጋገር ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነቱን በማረጋገጥ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ደግሞ ሕጋዊም ተገቢም ነውና ይበል የሚያሰኝ ነው!

እፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73
ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## "በ'97 የተመዘገባችሁ ..."

ግርማ (MaR)

ከመሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች አንዱ ነው። ሰው ሰው በመሆኑ ብቻ ሊኖረው የሚገባ ጉዳይ ነው። ሰው በዜግነቱም ሆነ ሰብዓዊነቱ የዚህ መሠረታዊ ሰብዓዊ መብት ተጠቃሚ የመሆን ሙሉ(ወይም፣ ያልተሸራረፈ) መብት አለው። ይህንን ስንል ግን ግዴታውን አሟልቶ ሲገኝ ነው።

ከላይ ግዴታውን (መስፈርቱን አላልንም፤ ምክንያቱ ደግሞ መስፈርት እንደየግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ ርዕዮቶች ... ስለሚለያይ) ስንል ልክ እንደ መሰሎቹ ማግኘት የሚያስችለውን ግዴታ አሟልቶ ከተገኘ እንዳያገኝ የሚያደርገው ምንም አይነት ምድራዊ ኃይል "የለም" ማለት ነው።

"በ'97 የተመዘገባችሁ ..." የሚለው ርዕሳችን ጥሪ ከመሰለ ይቅርታ እየጠየቅን ጥሪ አለመሆኑን እንገልፃለን። ጥሪ አለመሆኑን ስንገልፅ ግን በ2015 ዓ.ም ሳይቀር "በ'97 የተመዘገባችሁ ..." ማለቱ ከማንኛውም መመዘኛ አኳያ ሲታይ የሚያስኬድ አለመሆኑን በመግለፅ ብቻ ሳይሆን፤ ኢትዮጵያን ከመሰለና የጠንካራ መንግሥት ባለቤትና ተምሳሌት ከሆነ አገር (እንድገመውና በ2015 ዓ.ም) "በ'97 የተመዘገባችሁ ..." የሚለው እማይጠበቅና እማይመጥናትም ጭምር መሆኑንም በመግለፅ ነው።

ይህንን ካልን ወደ አንድ ታሪካዊ ጉዳይ እንሂድና ተሞክሮዎችን እንመልከት - American Dream። (ላይ ላዩንም ቢሆን) በቀላሉ መረዳት እንደሚቻለው American Dream የአሜሪካ ሕልም ነው። ሀገር እንደ ሰው ሕልም ያየበት፣ ራዕይ የሰነቀበት .... መሆኑ ነው።

ይህ በእነሱ አቆጣጠር በ1931 ለአደባባይ የበቃውና ወደ ሥራ ቋንቋነት የተቀየረው American Dream ዋና ተዋንያኑ ሰዎች ሲሆኑ፤ እነሱም አሜሪካውያኑ ናቸው። የሕልሙ ዓላማም አሜሪካውያንን የሁሉም ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች፤ በተለይም የመኖሪያ ቤት(ቶች) ተጠቃሚ (ሰነዱ "owning your own house" ነው የሚለው) በማድረግ አሜሪካንን የበለፀገች ማድረግ ነው። (ዝርዝር ታሪኩን ከየትም መረዳት ስለሚቻል እንዝለለው።)

ይህን፣ በመዝገበ ቃላት(ዲክሽነሪ) የተካተተን ፅንሰ ሀሳብ አክስፎርድ ፍቺ የሰጠው ሲሆን፣ በፍችውም ግዴታዎችን (hard work, determination, and initiative) አካትቷል። እነዚህን ያሟላ ሁሉ ወደ ብልፅግና ማማው መረማመድ የሚችል ሲሆን፤ አሠራሩ ለአድሏዊነት፣ ወገናዊነት ... ምንም አይነት በር እንደ ሌለ ያመለክታል።

እንግዲህ የቤት ባለቤት (የመንግሥት ቤቶች ፕሮግራም ተጠቃሚ) ለመሆን ጥያቄው የተጠቀሱትን ግዴታዎች ሟሟላት ነው።

የቤት ፕሮጀክቱን፣ ፕሮግራሙን፤ ለዛውም የቆመበት መሠረት "ለደሀው ..." የሆነውን ... ድብን ያለ የ... መሣሪያ ማድረግ፣ የችግሩ ገፈት ቀማሾች እንደሚሉት "በምድርም በሰማይም ያስወቅሳል፤ ያስጠይቃልም።" ይህ ግን የሚሆነው ወቃሽም ጠያቂም ሲኖር እንጂ ከሌለ "በ'97 የተመዘገባችሁ ..." ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። ከአጠቃላይ የግንባታ ፕሮጀክቶች አኳያ ወደ ዛሬይቱ ኢትዮጵያ እንምጣ።

እንደሚታወቀው፣ ኢትዮጵያ ይህንንም ሆነ ሌሎች (ሜጋዎችን ጨምሮ) ፕሮጀክቶችን (ለምሳሌ የስኳር) በተመለከተ የጥቂቶች የገቢ ምንጭ ይሆኑ ዘንድ ሆን ተብሎ፣ በእቅድ የተሠራ እስኪመስል ድረስ (ካልሆነ ማለት ነው)፣ መፈንጫ ሆና እንደ ነበር ከሀገራዊ ለውጡ ማግስት የወጡ መረጃዎች ያመለክታሉና እነሱን መለስ ብሎ መቃኘት ነው። ከዛ ወዲህስ?

ሁላችንም እንደምንመለከተው ከለውጡ ማግስት የግንባታ ፕሮጀክቶች ለማመን በሚያቅት ደረጃ ሁሉ ጥሩ አፈፃፀምን እያሳዩ ነው (ለዛውም ጥራትን ከውበት ጋር - ይህ የባለሙያ አስተያየት አይደለም)። ይህንን ለማረጋገጥ 1፣ 2፣ 3 ... እያሉ ከመዘርዘር ይልቅ በቀላሉ ለመናገር ከመስቀል አደባባይ ተነስቶ፣ በአራት ኪሎ አድርጎ ወደ እንጦጦ ማቅናቱ ብቻ ለማሳያነት በቂ ነውና በዚሁ ማለፍ ይቻላል። ያንሳል ከተባለም፣ ከእንጦጦ ወደ ፒያሳ ወረድ ብሎ የአድዋውን "ዜሮ ፕሮጀክት" መመልከት ነው፤ ተስፋን ሁሉ ያጭራል። ችግሩ፣ ድህረ ዐቢይ አስተዳደር የግንባታ አመራርም ይሁን አሠራር በእነዚህ እየታየ ያለው ለውጥ ለምን ወደ ኮንዶሚኒየሙ ዘርፍ ጎራ ብሎ፣ ከተማዋ አስተዳደር የሌላት የሚያስመስለውን "በ'97 የተመዘገባችሁ ..." አገላለፅ ለማስቀረት፤ ተረት የማድረግ፣ በዘርፉ ያለውን ... ለመፍታት ጥረት አላደረገም ነው።

ዛሬ፣ ምንም እንኳን የመኖሪያ ቤት ችግር የትም አገር ያለ ቢሆንም፣ የተሻለ አፈፃፀም ያሳዩ ሀገራት የሉም ማለት አይደለም፤ ሞልተዋል። ደቡብ አፍሪካ እኮ የአጠቃላይ ሀገሪቱን የቤት ችግር የፈታችው በ5 ዓመት የልማት ፕሮግራም ነው፤ ፊሊፒንስ በተሻለ ምሳሌነት የምትጠቀስ አገር ነች። መጥቀሱ ቤት አይሠራም እንጂ ብዙ መጥቀስ ይቻላል።

አንድ ጠንካራ መንግሥት ያላት ሀገር ውስጥ፣ ያልተቋረጠ አስተዳደር ባለቤት የሆነች አገር ውስጥ፣ የከተማ ውስጥ የባቡር መስመርን በ5 ዓመት የገነባች ሀገር ውስጥ፣ ... ውስጥ፣ .... ውስጥ ...፤ እንዴት በ2015 ዓ.ም "በ'97 የተመዘገባችሁ ..."ይባላል? ነው ወይስ "ምርጫ 97"ን እናስታውስ ይሆን? (ወይስ ዓመቱ፣ በዓመታት ታሪክ ውስጥ ባለ ታሪክ ሆኖ ይታወስ፣ ይዘከር ... ዘንድ ታስቦለት? ጉዳዩ (ነፍሳቸውን ይማረውና) አማረ ማሞ "... ያወያያል፣ ያነጋግራል፣ ያመራምራል" እንዳሉት ነውና እኛም ይህንኑ እንላለን።)

በዚህ ጸሐፊ እምነት፣ 2015 ዓ.ም ላይ ሆኖ አይደለም 2005 ዓ.ም ላይ ሆኖ እንኳን "በ'97 የተመዘገባችሁ ..." ማለት ኢትዮጵያንና አስተዳደሯን አይመጥንም፤ ለማንኛውም አካል ቢሆን ከደረጃ በታች ነው። 2015 ላይ ሆኖማ፣ ጭራሽ ኢትዮጵያን ለ20+ ምናምን ዓመታት ያለ መንግሥት የኖረችውን ሶማሊያን እንኳን አይመጥንም። ስለዚህ?

ስለዚህ በ2020 ዓ.ምም "በ'97 የተመዘገባችሁ ..." የሚለው ዜና በዛን ሰዓት "ዓበይት ዜናዎች" ሆነው ከሚታወጁት አንዱ እንዳይሆንና የዛን ዘመን ጋዜጠኞች (የዛሬ ተማሪዎች) "በ'97 የተመዘገባችሁ ..." የሚለውን በአስገምጋሚ ድምፃቸው እንዳያሰሙን ማድረግ ያስፈልጋል። ነገሩ ከማማረርና ማሳዘን አልፎ ወደ "ሳቅ ጨዋታ"ነት እንዳያዘነብልብን እንቋጨው።

በምንም መልኩ አሁን ያለው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ቁመና ለኮንዶሚኒየም ግንባታ እና "በ'97 የተመዘገባችሁ ..."ን ለማስቀረት (ተረት ለማድረግ) አይሰንፍም። በምንም መንገድ በአዲስ አበባና ሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች እየተገነቡ ያሉ ግንባታዎችን በጥሩ ሁኔታ እያጠናቀቀች ላለች ሀገር ይሄ "ኮንዶ" የሚባለውን በመገንባት፣ ይሄ መጪውንና አዲስ ተመዝጋቢውን ትውልድ ተስፋ የሚያስቆርጥ አሠራር፣ "በ'97 የተመዘገባችሁ ..."ን ከስሩ በመንቀል ተረት ማድረግ አያቅታትም። ይህንን ስንል ኮንዶሚኒየሙን ቁጭ ቁጭ ማድረግ ቢያቅታት ኖሮ የመጀመሪያውን ዙር ባልገነባች ነበርና ነው። "ያቅታታል" ካልን ግን ኢኮኖሚያችን የመጀመሪያውን ዙር ኮንዶሚኒየም ስንገነባ ከነበረበት ወርዷል እያልን ነው ማለት ነውና ብዙ ነገሮች ይጣረሳሉ።

በመጨረሻም፣ ከላይ American Dream እንዳልነው ሁሉ "በ'97 የተመዘገባችሁ ..." እየተባሉ የሚጠቀሱት ሁሉ (ቢያንስ በሕይወት ያሉት) ሕልማቸው እውን ሆኖ ያዩት ዘንድ፤ "በ'97 የተመዘገባችሁ ..." ይሉ አባባል ተረት ይሆን ዘንደ እንመኛለን!

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

## «ተጠያቂነት የታለ የሚል ተደጋጋሚ የሕዝብ ጥያቄ አለ»

- አቶ ጥላሁን ሮባ
የለሚኩራ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ

ምሕረት ሞገስ



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደ ከቦሌእና ከየካ ክፍለ ከተሞች ቀንሶ አዲስ የተቋቋመው የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ከመልካም አስተዳደር ጋር ተያይዞ ከህብረተሰቡ የሚነሱ የተለያዩ ጥያቄዎች አሉ።ከጥያቄዎቹ መካከል የተወሰኑትን በማንሳት በተለይም በክፍለ ከተማው አለ ስለሚባለው የመሬት ወረራ እና የፋይል መጥፋት ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ከዋና ሥራ አስፈፃሚው አቶ ጥላሁን ሮባ ጋር ቆይታ አድርገን በዛሬው የ‹‹ተጠየቅ›› ዓምዳችን ላይ እንደሚከተለው ለንባብ አብቅተነዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በቅድሚያ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ እናንተ ሕዝቡን ይቅርታ ጠይቃችሁ ወደ ሥራ ከገባችሁ ነሐሴ 16 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የተሰራውን ሥራ ይግለፁልንና ቃለምልልሳችንን በዚህ እንጀምር።**

**አቶ ጥላሁን፡-** የከተማ አጠቃላይ ከፍተኛ አመራር በመሬት እና መሬት ነክ አገልግሎት አሰጣጦች ላይ የነበሩ ብልሹ አሠራሮችን ሲከታተል ስለነበር፤ ጉዳዩን አይቶ ፈጥኖ እርምጃ ወስዷል።አመራሮችን ቀይሯል።እኛም ወደ ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ከመጣን ወዲህ ቅድሚያ የሠጠነው ሥራዎችን መለየት ላይ ነው።መሬት ልማት ማኔጅመንት ላይ ልምድና ቁርጠኝነት ያላቸውን አመራሮች ተክተናል።በዚሁ መሰረት ስራችንን ስንጀምር መጀመሪያ አገልግሎታችንን ለማሳለጥ ችግሮችን መለየት ላይ አተኩረናል።

የተተኩ አመራሮች ከሰራተኞች ጋር በመወያየት እና ችግሮችን በመለየት ወደ ተግባር ስራ ገብተዋል።በዛ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በክፍለ ከተማው ሊሠሩ የሚገቡት ሥራዎች ላይ ከአመራር፣ ከአርሶ አደርና ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር መድረክ በመፍጠር ተወያይተናል።በአጭር ጊዜ ሊፈቱ የሚችሉ፣ ዕቅድ የሚያስፈልጋቸው፣ በረዥም ጊዜ መፈታት ያለባቸውን ለመለየት ያስቻለ መነሻ ላይ ደርሰናል።

**አዲስ ዘመን፡- በእርግጥ አሁን ላይ በተጨባጭ የተገኘውን ለውጥ ለመለካት ቢያዳግትም በዋናት የሚጠቀሰው ችግር የመሬት ጉዳይ ሲነሳ ከፋይል ጋር ይያያዛል።ፋይል ማደራጀትን በተመለከተ €€ ፋይል ጠፋ« የሚለውን የሙስና በር ለመዝጋት ምን ያህል ሔዳችሁበታል?**

**አቶ ጥላሁን፡-** በቅድሚያ መሥራት ያለብን ሰው ላይ መሆን እንዳለበት አምነናል።ሰው ላይ ሲባል ደግሞ ፋይሉን በተመለከተ ሊሠሩ የሚገባቸው ፈፃሚዎች ላይ ማለት ነው።የሥራ ክፍሎችን በመለየት ምን ጥንካሬ አለ? ምን እጥረትና ክፍተት አለ? የሚለውን በደንብ መለየት ላይ አተኩረናል።

ሌላው የትኛው የስራ አካባቢ ነው እንግልት እና ምልጃ ይጠየቅበታል? የሚለውን ለመለየት የመሬት ልማት ማኔጅመንትን ሥራ አቁመን ነበር።አሁን የጀመርናቸው እና መልሰንም ያቆምናቸው አገልግሎቶች አሉ።አንደኛው አርሶ አደር እና ከአርሶ አደር ጋር በተያያዘ መብት ፈጥራ፤ የይዞታ ባለቤትነት የተመለከተ ጉዳይ ነው።‹‹በከፍተኛ ደረጃ በደላሎች እየተዘረፍን ነው›› የሚለው በየመድረኮችም በሰፊው ሲነሳ ነበር።ይህ እስከ ሚጣራ ድረስ ይቆይብለናል።ስለዚህ አሁን የአርሶ አደር ይዞታ አገልግሎት አሰጣጥ ጉዳይ ቆሟል።

በሌላ በኩል የልማት ተነሺዎች ጉዳይም ግልፅ አይደለም።አንዱ ሌብነት የሚፈፀመው በልማት ተነሺ ስም ነው።ሁሉም የልማት ተነሺ ሌባ አይደለም።ነገር ግን ከዛ ጋር ተያይዞ አንዳንዶች ሳይገባቸው አብረው መጥተው መብት የሚያገኙበት ሁኔታ አለ።የሚል ሃሳብ በውይይቶች ስለተነሳ እና ይህንንም የሚያመለክቱ መረጃዎች በመኖራቸው፤ በዚህ ላይ ለጊዜው አገልግሎት ከመስጠት ለመቆጠብ ተገደናል።ስለዚህ 2011 ዓ.ም፣ 2012 ዓ.ም፣ 2013 ዓ.ም እና 2014 ዓ.ም ካርታ የወጣባቸውንና የልማት ተነሺዎች ላይም አገልግሎት መስጠትን በሚመለከት ለጊዜው የማቆየት ውሳኔ ላይ ተደርሷል።

**የ**ልማት ተነሺዎች ጉዳይም ግልፅ አይደለም። አንዱ ሌብነት የሚፈፀመው በልማት ተነሺ ስም ነው። ሁሉም የልማት ተነሺ ሌባ አይደለም። ነገር ግን ከዛ ጋር ተያይዞ አንዳንዶች ሳይገባቸው አብረው መጥተው መብት የሚያገኙበት ሁኔታ አለ። የሚል ሃሳብ በውይይቶች ስለተነሳ እና ይህንንም የሚያመለክቱ መረጃዎች በመኖራቸው፤ በዚህ ላይ ለጊዜው አገልግሎት ከመስጠት ለመቆጠብ ተገደናል

ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ አልዘጋንም ነባር ይዞታዎች ላይ በክርክር በፍርድ ቤት አገልግሎት ማግኘት ለሚፈልጉ ነዋሪዎች አገልግሎት እየሰጠን ነው። አስቸጋሪ የሆኑትን እያጣራን ነው።እዚህ ላይ ጎን ለጎን ደግሞ ሁሉም ይዞታዎች በዲጂታል እንዲሆኑ እንፈልጋለን።ዲጂታል ሲሆኑ የፋይል መጥፋት እና መደራረብ ላይ ችግር የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን በቴክኖሎጂ ተመሥርተን እንቀንሳቸዋለን ብለን የአጭር ጊዜ ዕቅድ ይዘናል።

አገልግሎት የሚሰጥበት በታም ምቹ ያለመሆን ሁኔታ ነበር።ይህንን በማስተካከላችን የፋይል መዝረክረኮች ፈር እየያዙ ነው።ሁለተኛው ሩብ ዓመት ላይ በተሻለ እና በተደራጀ ሁኔታ እንጨርሳለን።አጠቃላይ እስከ አሁን አንደኛው ሩብ ዓመት የቻልነውን እየጨረስነው ነው።

ለአርሶ አደሩም አገልግሎት የመስጠት ጉዳይ ተዘግቶ አይቆይም።ትክክለኛ አርሶ አደሮችን እያጠራን እየለየን ነው።በትክክል ከደላላ ነጻ የሆነ ራሱንና ራሱን ብቻ የሚገልጽ አርሶ አደር ነው ወይ? በማለት አርሶ አደሮችን እየለየን የማጥራት ሥራ እየሠራን ነው።በዚህ ሂደት በስኬት እየሔድን ነው።ሲጠናቀቅ የደረስንበትን መሬት ልማት ማኔጅመንት ይሔድበታል።

መሬት ልማት ማኔጅመንትም ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ከሰራተኞቹ ጋር በቅርበት በመነጋገር ችግሮቹን እየለየ የሚያንገላታው ማን ነው? በማለት እየገመገሙ እስከ ምሽት ሥራቸውን ይሠራሉ።በየዕለቱ ተግባራቸውን ይገመግማሉ፤ በዚሁ መሠረት የማጥራት ሥራ እየሠራን ነው።ከዚህ በተረፈ ወደ ሕግ በመሔድ ተጠያቂነት መኖር ካለበትም ከግኝት በመነሳት ወደ ተጠያቂነት እናመራለን።ማንም ቢሆን አመራርም ሆነ ፈፃሚ መጠየቅ ያለበት ይጠየቃል።

ታጭቀው የነበሩ የተለያዩ ምቹ ያልሆኑ አሠራሮችን ቅድሚያ በማስወገድ እየሔድን ነው።መጠነኛ መሻሻሎች መኖራቸው በተገልጋይ አስተያየቶች ላይ እየተገለፀ ነው።በኮሙኒኬሽን በኩል እያንዳንዱ ተገልጋይ ሲመጣ ምን አስተያየት አለ? ምን እናሻሽል? እያልን አልፎ አልፎ ተገልጋይን እየዞርን እናነጋግራለን።ይህንን ማድረጋችንም የተገልጋዩን ፍላጎት ለማወቅ እያገዘን ነው።ተገልጋይም በበኩሉ ‹‹በርቱ ቀጥሉ›› በማለት ላይ ይገኛል።አንዳንዴም ችግር ያለባቸው አካላት አሁንም ሲመጡ በማየታቸው ለምን ተጠያቂ አይሆኑም የሚሉ ሃሳቦችን ይሰነዝራሉ።ተጠያቂነቱ የታለ የሚል የሕዝብ ተደጋጋሚ ጥያቄ አለ።ይህንን በማስረጃ እና በመረጃ አስደግፈን በተደራጀ መልኩ የምንሔድበት ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ጥያቄውን ከፋይል ጋር ያያዝኩበት ምክንያት ብዙ ጊዜ የመልካም አስተዳደር ችግር እና ሙስና የሚፈፀመው ከፋይል ጋር ተያይዞ በመሆኑ ነው።በክፍለ ከተማችሁ ለጠፋ ፋይል ከ1 ሺህ እስከ 5 ሺህ ብር የሚጠየቅ ስለመሆኑ ይወራል።ፋይል ሲጠፋ ፋይሉ ሲገኝ እንደውላለን በሚል ሰበብ ስልክ ቁጥር ወስዶ መደራደር ስለመኖሩም ይነገራል።ስለዚህ ምን ትላላችሁ?**

**አቶ ጥላሁን፡-** እዚህ ላይ በትኩረት በመስራት ላይ ነን።ከየካ እና ከቦሌ ክፍለ ከተሞች ተቀናጅቶ 160 ሺህ ፋይል እዚህ ተመስርቷል።ርክክብ ስናደርግ ቀደም ሲል ፋይል ተደራጅቷል ብለው ያሳዩን ትክክል አልነበረም።በአንድ አቃፊ ውስጥ ሁለትና ሶስት ፋይሎች ነበሩ።በአንድ ሰው ስም ፋይሉ ሲፈለግ አይገኝም ነበር።ይህንን በአጭር ጊዜ ለመፍታት ያስቸግራል።

በሁለተኛው ሩብ ዓመት ላይ በዲጂታል ካደረግን 160ሺህ ፋይልን በአጭር ጊዜ ማደራጀት ያስቸግራል።ስለዚህ ሥራው ቦታውን ምቹ ከማድረግ ይጀመራል።በከፍተኛ ሥራ በሁለት ወር ውስጥ እናከናውነዋለን ብለን አስበናል።ነገር ግን ይህ ያለንበት ሕንፃ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የተደባለቀ እና ለአገልግሎት አሰጣጥም ምቹ ባለመሆኑ ያ ይስተካከላል።

ሌሎች ክፍለከተሞች የመሬት ልማት ማኔጅመንት ቢሮ ሕንፃው የተለየ ነው።ይህ ግን ከሌሎች ዘርፎች ጋር የታጨቀ በመሆኑ ለማስተካከል ያስቸግራል።ቢሆንም ሌሎች ሕንፃዎችን በኪራይ በማመቻቸት አሁን የምንለውን ፋይሎችን ዲጂታል በማድረግ መደራደር እንዳይኖር እናደርጋለን።በእርግጥ አሁን ባለው ሁኔታ ስጋቶች አሉ።ለዚህም ተነጋግረናል።ሆኖም ግን አሁንም ሙስና ተፈፀመ ከተባለ ወዲያው እርምጃ እንወስዳለን።አሁን ላይ ግን ሙሉ ለሙሉ የመልካም አስተዳደር ችግር የለም ፤ ዜሮ ሆኗል የሚለውን አናውቅም።

አሁን ለአገልግሎት አሰጣጥ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል።መዘግየት ሲኖር የቅርብ አለቃም ሆነ እኛ እንሰማለን።ስለዚህ ለመደራደር ያለው አቅም አነስተኛ ነው።አገልግሎት በሚሠጥበት ጊዜ የሠራተኛው ቁጥር ውስን በመሆኑ ሊራዘም ይችላል።ይህ ወደ ፊትም ያጋጥማል።ነገር ግን መደራደር ስልክ ቁጥር መያዝና ለፋይል ተመን ማውጣት የለም።ነገር ግን ዜሮ ሆኗል? የሚል ጥያቄ ከቀረበ ያንን ለመግለፅ ያዳግታል።

**አዲስ ዘመን፡- እናንተ ወደ ስራው ከመጣችሁ በኋላም ሆነ በፊት ባለሙያም ሆነ አመራር ላይ የወሰዳችሁት ሊገለፅ የሚችል እርምጃ አለ?**

**አቶ ጥላሁን፡-** የመጀመሪያ ሥራው የፖለቲካ እርምጃ ነው።የመሬትን ሥራ ሲመሩ የነበሩት ላይ ከሹመት የማውረድ ሥራ ተሠርቷል።ይህ ማለት እኛ ስንረከብ ሁለቱ ሃላፊዎች ተነስተዋል።ከችግሩ ጥልቀት አንፃር የተወሰነ ሃላፊን በማንሳት ብቻ ሳይሆን ተጠያቂነትን በማስፈንም ጭምር የሚያስጠይቅበት ሁኔታ ሲኖር ደግሞ ባለፈው አንድ ወር ባገኘነው ግኝት እና በአጭር ጊዜ እየተጠኑ ባሉ ሁኔታዎች ወደ ፈፃሚም የሚወርድበት ሁኔታ ይኖራል።በቅድሚያ ግን አመራር በማንሳት ያንን ሊመራ የሚችል ዕውቀት ያለው አመራር ተክተናል።የመጀመሪያው እርምጃ እርሱ ነው።

ሁለተኛው አመራሮቹ ከተነሱ በኋላ ማንም ፈፃሚ አልገባም።አሸገን ነገሩ እስከሚገመገም እና ችግሩ እስከሚለይ የትኛውን አገልግሎት ብንጀምር ይሻላል የሚለውን እስከምንለይ ድረስ ሰራተኛውን አላስገባንም።በኋላም ሕዝቡን ስላቆየን ይቅርታ ጠይቀን ለማስጀመር ሞክረናል።

**አዲስ ዘመን፡- ለሚ ኩራ ላይ ካርታ መከነ የሚል ወሬ ይናፈሳል፤ በማህበራዊ ሚዲያም ሆነ በአንዳንድ መገናኛ ብዙሃን ይገለፃል።ካርታ የሚመክነው ለምንድን ነው?**

**አቶ ጥላሁን፡-** አሁን እኛ እያጠራን ነው።ከላይ የገለፅኳቸው የአርሶ አደርን ጉዳይ ስናይ አርሶ አደር ሳይሆኑ እዚህ የገቡ በተለይ እኛ ከመጣን በኋላ የሉም።ነገር ግን ውጪ የሚሰሩ ካርታዎች ስለመኖራቸው መረጃ ይደርሰናል።ውጪ አሉ ማለት እኛ ጋር ወደ ፋይላችን ይገባሉ ማለት አይደለም።ነገር ግን ቀደም ሲል በዛ መልክ ተዘጋጅተው ወደ እኛ ፋይል የገቡ አሉ።ይህንን ለማግኘት የአርሶ አደርን መረጃ እያጠናን ነው።

ሁለተኛ የልማት ተነሺ እና ሌሎችንም ኦዲት ማድረግ እየጀመርን ነው።እርሱ ሲጠናቀቅ እነዚህ ካርታዎች ባለቤት የላቸውም፣ እኛን አይገልፁም፣ በአግባቡ ተደራጅተው የመጡ አይደሉም እያልን ብዛታቸውም ይህን ያክላል ብለን እናስወግዳቸዋለን።ነገር

# ተጠየቅ



ግን ከዚህ በፊትም መቃጠል እና መወገድ የነበረባቸው ተከማችተው የነበሩ፤ አንዳንዴም ለሌላ አሰራር ሲያጋልጡ የነበሩ የመሬት ልማት አመራሮች እዛ አካባቢ ከተወከሉ በኋላ በአደባባይ አቃጥለናል።ይሔም እዚህ የተቀመጡ ከኋላ እየታዩ የሚሰሩ ካርታዎች መኖራቸውን በተመለከተ መረጃ ስላለን ነው።በተጨማሪ በከተማ አስተዳደር ደረጃም የተቀመጠ አቅጣጫ ነበር።

ካርታዎቹ አዲስ ናቸው።ተከማችተው ያሉ ነገር ግን ለፎርጂድ መስሪያ ይውላሉ በማለት የከተማ አስተዳደሩ ማስወገድ አለብን ባለው መሠረት ተቃጥለዋል።ይሔ በሌሎች ክፍለከተሞችም የተፈፀመ ሲሆን በይፋ ሁሉም ባለበት የተቃጠለ ነው።

**አዲስ ዘመን።- በክፍለ ከተማው ያሉ ክፍት ቦታዎች ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የሚያዙበት ሁኔታ ስለመኖሩ ይነገራል።እርሶ ግን በትክክል ደንብ የማስከበር ሥራ እየተሠራ ነው ብለው ያምናሉ።**

**አቶ ጥላሁን።-** አሁን እኛ ከመጣን ወዲህ ሌሊትም ሆነ ቀን በማንኛውም ሰዓት ቢታጠር እርምጃ የሚወሰደው ወዲያው ነው።በየዕለቱ አሰሳ ይደረጋል፤ በግብረሃይልም ግምገማ ይደረጋል።በየዕለቱ ለሰላምና ፀጥታ ሕዝቡን በማደራጀት ደረጃ እንቅስቃሴ ይደረጋል።በቀደም ወረዳ አንድ ላይ አንድ ሔክታር የሚሆን መሬት በሌሊት ሲታጠር መረጃ ደረሰን፤ ወዲያውኑ ሄደን በቦታው ተገኝተን አስቁመናል።ሌሎችም በዓልን አስታከው የሚያጥሩ ነበሩ።ወዲያው መረጃው እንደደረሰን እርምጃ እንወስዳለን።

ክፍት ቦታዎች አሉ።ቦታዎቹ ግን አብዛኛዎቹ ለኢንቨስትመንት የሚውሉ እና ከተማው የሚወስናቸው ናቸው።በከተማው መሬት ልማት ማኔጅመንት ከዛም በካቢኔው ውሳኔ ለኢንቨስትመንት እና ለተለያዩ ተቋማት በዕውቀት ላይ በተመሰረተ መልኩ ይሰጣሉ።ሌላው ደግሞ አስተዳደሩ ራሱ የሚያስገነባቸው ተቋማት አሉ።እኛ ራሳችን ቢሮ የለንም።ወረዳዎቹ፣ ወጣት ማዕከላቱ፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ትምህርት ቤቶች እነዚህ ሁሉ ቦታና ግንባታ ይፈልጋሉ።ስለዚህ ከላይ ካልናቸው ‹‹የልማት ተነሺዎችና አርሶ አደር ነን›› ብለው በአርሶ አደር ስም የታጠሩ ቦታዎችን አሁን በማጥራት ሒደታችን በህገወጥ መንገድ

> **በቤተ እምነት ስም ቦታን ማስፋፋት እና ለእምነቱ ሳይሆን ለሌላ ዓላማ የመጠቀም ሁኔታ አለ። በእምነት ተቋም ውስጥ ሽብርተኛን ሲያሰለጥኑ፣ መሳሪያ ሲያከማቹ የተያዙ አሉ**

ይዘው የተገኙ ከሆነ እርምጃ እንወስዳለን።

ማንም ሰው የሕዝብ እና የመንግሥት ንብረትን ማንም ሰው ከመሬት ተነስቶ መውሰድ አይችልም።ዋናው የሕግ የበላይነትን ማስፈን ነው።መሬት በፕላን የሚመራ ነው።ማንም እንደፈለገ አጥሮ የኔ መሬት ነው ብሎ ካርታ የሚያወጣበት አይደለም።ነገር ግን ይህ እንዴት ተሰጠ የሚለውን ከብሎክ ጀምረን እናያለን።በፍፁም ይህንን አንታገስም።ይህ የመንግሥት ቁርጥ አቋም ነው።ሕገወጦች ላይ እርምጃ እንወስዳለን።

ቀድመው ታጥረው የተገኙት ደግሞ ዝም ብለን በጅምላ ይፍረሱ ሳይሆን አሁን ባቋቋምነው አጣሪ ተጣርቶ የሚመክን ካርታ ካለ ይመክናል፤ መፍረስ ያለበትም ይፈርሳል።ባለመሬቱ ራሱ ካለ ደግሞ በመመሪያ መሰረት ይስተናገዳል።ሌላው ግን በእምነት ተቋማት ስም መጥተው መሬት የሚወሩበት ሁኔታ ፈተና ሆኖብናል።የእምነት ተቋማት ከጀርባቸው የእምነት ተከታዩ ሕዝብ አለ።ነገር ግን ሕዝቡ መሬት እንዲወረር ፍላጎት የለውም፤ ነገር ግን እነርሱ ሌላ ተልዕኮ ያላቸው፤ ይህንን ይፈፅማሉ።

**አዲስ ዘመን።- ቀጣዩ ጥያቄዬ ይህ ነበር።እንዳውም የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማው በተቋቋመ በጥቂት ጊዜ ውስጥ በክፍለ ከተማው በርካታ አዳዲስ ቤተዕምነቶች ስለመገንባታቸው ይነገራል።እንደውም ለአንድ ቤተ እምነት መገንቢያ ቦታ እጅ መንሻ እስከ 5 ሚሊዮን ብር ይሰጥ እንደነበርም ይገለፃል።ይሄ በእናንተም ግምገማ የታየ ነው ?**

**አቶ ጥላሁን።-** እንደተባለው ‹‹እጅ መንሻ ይሰጣል፤ ደላላም በስፋት አለ›› የሚለው ወሬ መዓት ነው።መሬቱ በትክክል ሙስና ተሰጥቶ ነው የተገኘው የሚለውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።ለቤተ እምነትም ሆነ ለሌላ መሬት እንዴት እንደሚተላለፍ መመሪያ አለ።ለትላልቅ ኢንቨስትመንት ብቻ ሳይሆን እኛ ራሳችን ‹‹ትምህርት ቤት መገንባት እንፈልጋለን›› ብንል ቦታውን ለይተን ወደ ከተማ አስተዳደሩ እንልካለን።

የከተማው መሬት ማኔጅመንት ይወያያል፤ ለካቢኔ ቀርቦ ውሳኔ ይተላለፍበታል።ይህንን ሒደት ጠብቀው ያገኙ የእምነት ተቋማት አሉ።የተለያየ እምነት ተከታይ ሕዝብ በክፍለ ከተማው አለ።የሚያመልክበት ቦታ ሊጠይቅ ይችላል።ስንት ካሬ ሜትር መጠየቅ ይችላል? ከተባለ በከተማ ደረጃ ይታወቃል።እዚህ ቦታ ላይ ይህን ያህል ካሬ ይሰጣቸው ይባላል።ነገር ግን አሁን ያለው ችግር የእምነት ተቋማት ቀድመው ቦታ በመያዝ ያንን ቦታ እንዲፈቀድ የማድረግ ሁኔታዎች አሉ።

እንደውም አንዳንድ የእምነት ተቋማት በካቢኔ ተወስኖላቸው ሕገወጦች ይዘው አንለቅም ያሉ አሉ።እነዛ ‹‹ሕግ ይከበርልን›› ብለው የጠየቁ አሉ።አንዳንዱ ደግሞ የያዘውን እያሰፋ እና ሌላውን እያስለቀቀ ስለእውነት ያ ቦታ ለእምነት ቦታ የተፈቀደ ነው ወይ? ሲባል በፕላን ለትምህርት ቤት ወይም ለሌላ ዓላማ የተዘጋጀን ቦታ ቤተ እምነት ይገነባሉ።ወይም የማስፋፋት ሕግ ለማስከበር ሲኬድ ደግሞ ከእምነት ጋር የማያያዝ ሁኔታ አለ።በእርግጥ ሕዝቡ የሚያቀርባቸው ቅሬታዎች አሉ።በእርግጥ እነዚህ የእምነት ተቋማት የራሳቸው ካርታ አላቸው ወይ? በማለት በተፈቀደላቸው ቦታ ላይ ናቸው ወይ? የሚለውን ማጣራትን ይጠይቃል።

አሁን ግን ቅድሚያ የማጣራት ስራ የምንሰራው የአርሶ አደሩን እና የልማት ተነሺውን ጉዳይ ነው።የእምነት ተቋማት አጥር ራሱ በከተማ አስተዳደር ደረጃ እንጂ በእኛ ደረጃ አይፈቀድላቸውም።ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት በቤተ እምነት ስም ቦታን ማስፋፋት እና ለእምነቱ ሳይሆን ለሌላ ዓላማ የመጠቀም ሁኔታ አለ።በእምነት ተቋም ውስጥ ሽብርተኛን ሲያሰለጥኑ፣ መሳሪያ ሲያከማቹ የተያዙ አሉ።ይህንን የማንም እምነት አይፈቅድም።ሁሉም የእምነት ተቋማት መሪዎች በጉዳዩ ላይ በጥንቃቄ ማሰብ አለባቸው።ስሜታዊ የሚያደርግ ቢሆንም ሕግን ማስከበር ደግሞ ተገቢ ነው።

**አዲስ ዘመን።- በክፍለ ከተማው ቀድሞም በነበሩ መኖሪያ ቤት አካባቢዎች ለአረንጓዴ ልማት እና ለነዋሪው መናፈሻ ቦታዎች ታስበው የተተዉ ቦታዎች አሉ።እነዚህን ቦታዎች ግለሰቦች የሚወሩበት ሁኔታ እንዳለ እየተነገረ ነው።ለምሳሌ ሻይ የሚያፈሉ አስመስሉ ሸራ መወጠር ከዛም አስፋፍቶ መያዝና ቀስ በቀስ እስከማጠር የሚደርሱ አሉ።እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ጥላሁን።-** ይህንን የሚጠብቅና የሚከታተል ፅህፈት ቤት አለን።አንዱ መሬት የሚያዝበት መንገድ አረንጓዴ ልማት በሚል ነው።የጋራ መኖሪያ ቤት ላይ የመስክ ነው ብለው ዛፍ እየተከሉ ቀስ በቀስ ይይዛሉ።ነገር ግን በፕላኑ ላይ መሬቱ ለአረንጓዴ ልማት ከሆነ ለአረንጓዴ ልማት መዋል አለበት።ከዛም አልፎ የመንገድ አካፋይን ሳይቀር የሚይዙ ሰዎች ይኖራሉ።ሕብረተሰቡም እንደመብት ይቆጥራል። አረንጓዴ ልማት በመንግሥት የሚለማ አለ። በግል አልሚዎች የሚለማ አለ።ምንም መቀየር ሳይኖር በዛው ልክ መጠቀም ያስፈልጋል።ከዛ ውጪ በአረንጓዴ ልማት ስም ይዘው የሚያካትቱትን ህብረተሰቡ ሊጠቁም ይገባል።እኛም ሕግ እናስከብራለን።

አደባባይን ሳይቀር ሻይ ለማፍላት እየተጠቀሙ የሚይዙ አሉ።ወረራው ትንሽ አይደለም፤ ብዙ ነው። ሕብረተሰቡ ደግሞ የሚጠቁም ከሆነ መሬቱ ለሌላ ዓላማ እንዳይውል ማድረግ የኛም ግዴታ ነው።ሕብረተሰቡም መከላከል አለበት።በተጨማሪ መሬት መያዝ በተለያየ መልኩ አለ።ብዙ ኮንደሚኒየሞች አሉ።ኮንደሚኒየሙን አጥሮ በመያዝ ማንም ወደዛ እንዳይገባ የማድረግ ሁኔታ አለ።ይሔ የአረንጓዴ ልማት ቦታችን ነው ይላሉ።ማን ሰጠ? የሚል ጥያቄ ሲቀርብ ምላሽ የለም።ለምሳሌ የሪል ስቴት አልሚዎች መሬቱን በሊዝ ገዝተው ከሚገነቡበት ውጪ ያለውን ይሔ መናፈሻ ነው ሊሉ ይችላሉ።በሊዝ ስለያዙ ይችላሉ።

**አዲስ ዘመን።- በክፍለ ከተማው ልዩ ስሙ 49 ማዞሪያ በሚባለው አካባቢ ባሉ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የ2011 ዓ.ም የ40 በ60 የቤት ዕድለኞች €€ቤቱ እጣ ከወጣበት ሶስት ዓመት አለፈ።መንገድ ባለመሰራቱ ፍሳሽ ማስወገጃው ከጋራ መኖሪያ ቤቶቹ ጋር አልተያያዘም።መንገድ እንዳይሰራ ደግሞ ካሳ አልተከፈለንም ያሉ ሰዎች የመንገድ መስሪያ ማሽን እናቃጥላለን በማለታቸው መንገዱ መሰራት አልቻለም።ክፍለ ከተማውም ጉዳዩን ማስተካከል ተስኖታል።« ሲሉ ይደመጣሉ ፤ በዚህ ላይ ምን ምላሽ አለዎት ?**

**አቶ ጥላሁን።-** በእርግጥ ጉዳዩን በቅርቡ ሰምቼዋለሁ።በአጋጣሚ አንድ መገናኛ ብዙሃን መጥቶ ሲጠይቅ ባለጉዳዮቹ ይምጡና ችግሩን እናየዋለን ብለናል። ጉዳዩን አናውቀውም ነበር።በክፍለ ከተማው ብዙ ችግሮች አሉ።ገና አሁን በእያንዳንዱ ላይ ውይይት ካላደረግን ችግሮችን አናውቃቸውም።ነገር ግን በየቀጠናውና በየወረዳው ውይይት እናደርጋለን። የሕብረተሰቡን ችግር ወደ ዕቅዳችን አስገብተን እንመልሳለን።

እነዚህ የጋራ መኖሪያ ቤት ሥራዎች በቅንጅት የሚሠሩ ሥራዎች ናቸው።በእርግጥ ቤቱ ተገንብቷል።አንዳንዶቹ ቁልፍ ተሰጥቷቸዋል።ነገር ግን እነሱ ሲያስረዱን ለመኖር የሚያስችል ምንም ምቹ ሁኔታ አልተፈጠረም።ምክንያቱም ፍሳሽ ማስወገጃ የለም።ሰዎች ከሌላ ቦታ ውሃ እንኳን ቀድተው ለመጠቀም ቢሞክሩ አይሆንላቸውም።ምክንያቱም ፍሳሽ ማስወገጃው መስመር አልተገናኘም።

እዛ አካባቢ እንደውም ፍሳሹ በሚያርፍበት ቦታ ቤቶች ተሰርተዋል።ሰዎቹ በእርግጥም እስከዚህ ደረጃ መድረስ አልነበረባቸውም፤ ምክንያቱም መንገዶች፣ ቤቶች፣ውሃና ፍሳሽ እና እኛ ሆነን መስራት ነበረብን።የእነዚህ ባለድርሻ አካላት ተቀናጅቶ ተገናኝቶ በሁለት ቀንም ይሁን በሳምንት ምላሽ ባለመስጠቱ ለዚህ ደርሰዋል።ነገር ግን በቅንጅት መሠራት አለበት።ሁላችንም ያጋጠሙ ችግሮችን እየገመገምን ችግሩን መፍታት አለብን።መንገድም፣ ውሃና ፍሳሽም፣ ቤቶችም ክፍለከተማውም ተቀናጅተን መስራት አለብን።

በእኛ በኩል በቦታው ላይ ሰዎች ካሉ እና ካሳ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ነዋሪ ስለመሆናቸው መረጃ ተደራጅቶ ለመሬት ልማት ቀርቦ ተረጋግጦ ይላክላቸውና ካሳ ይከፈላቸዋል።ሕገወጦች ከሆኑ ደግሞ ሕገወጥ ስለመሆናቸው ተረጋግጦ እርምት ይወሰዳል።የአካባቢውን ሰዎች አነጋግረናል ነገር ግን የብዙ ባለድርሻ አካላትን የያዘ ነው።ለወረዳዎችም እንዲያጣሩ ትዕዛዝ ሰጥተናል።

**አዲስ ዘመን።- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሰግናለሁ።ቶ ጥላሁን።-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# "ኑ እንዋቀስ!"- ማን ከማን?

**እንደ መንደርደሪያ ቢያግዘን፤**

"ኃያሲያን የሌሉት ሀገር ህመሙ ብዙ ነው" ይሉት ዓይነት አባባል በብዙዎች ዘንድ የተለመደ አነጋገር ነው። ብሂሉ የተሸከመው መልእክት የገዘፈ ብቻ ሳይሆን መገለጫውም በርከት ይላል። በምሳሌ እናመላክት ከተባለም አንዳንድ ማሳያዎችን መጠቋቆም ይቻላል። የማሕበረሰብ ሕይወት በዘርፉ ባለሙያዎች (Social critics) በሚገባና በጥልቅ ዐይን ይፈተሻል። የሀገር ሥነ ጥበብም ለሙያው ቅርበት ባላቸው "በባለ አራት ዐይናማ" ኃያሲያን (Art critics) እየተገመገመ "ጥሬው ከብስል" ይለያል።

ኢኮኖሚውና ፖለቲካውም በልሂቃኑ እየተመረመረ "እንዲህ አይሁን ወይንም እንዲህ ቢሆን ይሻላል" እየተባለ መፍትሔው ይጠቆማል። የየዘርፉ ድካምና ብርታት የሚጠቋቆመውና ህፀጾች እንዲታረሙ የሚደረግበት ዋነኛ ምክንያት የማሕበረሰብ ሕይወት ሳይኅመዘዝ እንዲጣፍጥና የተረጋጋና ሰላማዊ ኑሮ መምራት እንዲቻል በመቆርቆር ብቻም ሳይሆን ግዴታም ጭምር ስለመሆኑ ልብ ይሏል።

ይህ ጸሐፊ ላለፉት በርካታ ዓመታት በዚሁ ታሪካዊ ጋዜጣ ላይ የብዕሩ አቅም በፈቀደለት መጠን የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት በሀገሩ መልከ ብዙ ጉዳዮች ላይ የዜግነት ድርሻውን መወጣትን ቀዳሚ ዓላማው በማድረግ ሃሳቡን በነፃነት ሲያካፍል ኖሯል። እንደ አንድ ማሕበራዊ ኃያሲም መቀረፍ የሚገባው ሀገራዊ ችግር እንዲቀረፍ፣ መታረም የሚገባውም እንዲታረምና ውጤታማ ተግባራትም እንዲበረታቱ "ጫን ያሉ ሙግቶችንና አስተያየቶችን" በግልጽነት እየሰነዘረ በቤትኛነት መሰንበቱ ይታወቃል።

ዛሬም ቢሆን በማሕበራዊ፣ በኢኮኖሚውና በፖለቲካው አካሄዶችና ሥሪቶች ላይ የቢሆን ምኞቱንና የባይሆን ፍላጎቱን እንደ ሌሎች አቻ አምደኞች በዚህ ነፃ አምድ ላይ በነፃነት ከማጋራት አልቦዘነም። እውነታው ይህንን ቢመስልም የሀገራችን ችግሮች በሙሉ በዚህ ጸሐፊም ሆነ በመሰል ትጉሃን "ቀለም" ተጠቃቅሶ ተጠናቋል ለማለት አያስደፍርም።

ከጥቂት ዓመታት በፊት በየሚዲያው ሲተላለፍ እንደነበረው አንድ የምርት ማስታወቂያ ወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮቻችን ከዕለት ዕለት እየባሰባቸው "ጠብ ሲሉ ስንደፍን፣ ሲያንጠባጥቡ ስንደቅን" መኖራችን የሚካድ አይደለም። በሽታው ተፈውሶ ያልተጠናቀቀው ይህን መሰሉ ሀገራዊ ህመማችን መልኩም ሆነ ባህርይው ዝንጉርጉርና ውስብስብ ሆኖ ግራ እንዳጋባን መዝለቁ የእንቆቅልሻችንን ጥልቀት የሚያሳይ ነው።

የተጣቡን ጉልህ ሀገራዊ ችግሮቻችን መልካቸው ምን እንደሚመስል በውሱን ገለጻ ለመጠቋቆም እንሞክር። እየዳኸ ያለው ሀገራዊ ፖለቲካችን ከእንፉቅቁ ተላቆ ቢያንስ ቢያንስ ድክ ድክ ያለማለቱ ያሳስበናል። በልምሻ የተጠቃውን ይህን መሰሉን ደዌ የምህዳሩ ዋነኛ ተዋንያንና ኃያሲያን "ወፌ ቆመች፣ ወፌ ቆመች!" እያሉ በማበረታታት የላሸቀውን ጉልበታቸውን በመደማመጥ፣ በመከባበርና በመቀባበል እስካላጸኑ ድረስ መከራችን መራዘሙ አይቀሬ ይሆናል። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ብዙዎች ብዙ የመፍትሔና "የቢሆን ምኞታቸውን" ደጋግመው ቢገልጹም ሥር ሰዶ በደዌ የተጠቃው ፖለቲካችንና ህመምተኞቹ ፖለቲከኞቻችን ለፈውስ ከመሥራት ይልቅ እህህታንና ማቃሰትን ስለመረጡ እኛም ተራ ዜጎች በእነርሱ "ጦስና ጥንቡሳት" አሳራችንን ከመብላት ነጻ ልንሆን አልቻልንም።

ሀገሪቱ የተለከፈችበት የኢኮኖሚ አብሾም በነጋ በጠባ በማገርሸት ከእብደቱና ከወፈፌነቱ ፈውስ ማግኘት ስላልቻለ ዜጎችና ገበያው ሆድና ጀርባ ከሆኑ ሰነባብቷል። "በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተደምሮ" እንዲሉም የዓለም አቀፉ የምጣኔ ሀብት ሥርዓት በኢንፍሉዌንዛ ሲጠቃ በሀገራዊ ኑሯችን ላይ ጫናውን እያሳረፈ በማስነጠስ ወደ መኖርና አለመኖር አደጋ ላይ ጥሎ ሊጨፈልቀን የቀረው አንድ ሐሙስ ብቻ ነው። ያ "አንድ ሐሙስ" መቼ ሞልቶለት ቁርጣችንን እንደምናውቅ እርግጠኞች

> **"ፍትህን የምታጓድሉ፣ መደበኛ ተግባራችሁን ስትከውኑ ተገልጋይ የምታስለቅሱ፣ በንግዳችሁ እያጭበረበራችሁ ክብረትን የምትናፍቁ እንደ ጅማሬያችሁ ፍጻሜያችሁ ስለማያምር ቀኑ ሳይመሽባችሁ ፈጣሪ አምላካችሁ ኑና እንዋቀስ እያለ ጥሪ በማቅረብ ይጋብዛችኋል። በበደላችሁና በግፋችሁ የምትቀጥሉ ከሆነ ግን የምትመኩበት ሁሉ እንደ ጉም ይበናል፤ እንደ ትቢያም ከንቱ ይሆናል። ሳይመሽ በተሰጣችሁ ዕድል ንሰሃ ገብታችሁ ተመለሱ**

ስላልሆንን ኑሯችን ሁሉ "እንደ ምፀዓት ቀን" እንዳስፈራን ዛሬን ደርሰናል።

ከረጅም ዓመታት በኋላ የሚናፍቃትን የእናት አባቱን ሀገር ለማየት ዕድል ያገኘ አንድ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወጣት በቅርቡ በአንድ መድረክ ላይ ተገኝቶ በባእድ ቋንቋ ንግግር ሲያደርግ አድምጠነው ነበር። ይህ ወጣት ዲስኩሩን የደመደመው እንዲህ በማለት ነበር፤ "የኢትዮጵያ ሀገሬ አየር እንደ ዳቦ የሚገመጥ፤ የወገኖቼ ፍቅርም እንደ ሸማ የሚለበስ እንደሆነ በዐይኔ አይቼ ለማረጋገጥ ችያለሁ። " የሚለውን መልእክቱን አስተላልፎ እንደ ወረደ አንድ አባት ጎላ ባለ ድምጽ፡- "እውነት ተናገርክ የእኔ ልጅ። የኢትዮጵያ ሕዝብ እየኖረ ያለው በፈጣሪ ኪነ-ጥበብ አህል ሳይሆን አየር እየገመጠ ነው። ‹ሰው የሚኖረው በእንጀራ ብቻ ሳይሆን› አየር እየተመገበም ጭምር መሆኑ የእኛ ኑሮ ምስክር ነው። " በማለት የታዳሚውን ስሜት ኮርኩረው የምር አስቀውናል። እንደዚህ ጨርቁን ጥሎ ላበደው ሀገራዊ ኢኮኖሚያችን የዘርፉ ልሂቃንና ኃያሲያን መፍትሔውን አመላክተው ወደ ቀልቡ እስካልመለሱልን ድረስ የዜጎችን ናላ ያዞረው ወፈፍታው የሚያስከትለው ጉዳት በቀላሉ የሚታይ አይሆንም።

ከፉ ቀን የገጠመው አንድ አባወራ ኑሮ እንደ ወስከንባይ ተደፍቶበት ግራ ቢገባው ሚስቱን ለምንትስ ፈንጋዮች ለመሸጥ ተስማማ ይባላል። "ይባላል" መሆኑ ይያዝልን። ይሄው ግራ የገባው ባል ከፈንጋዮቹ ጋር በምሥጢር ተስማምቶ የተሸጠችውን ሚስቱን ራቅ አድርጎ ለመሸኘት አብረው ሲጓዙ ደግሞ ደጋግሞ "የቦርከና ወንዝ ማለት ይሄ ነው!" እያለ ይለፈልፍ ነበር አሉ። መልእክቱ "ምናልባት ዕድል ቀንቶሽ ከገዢዎችሽ አምልጠሽ የምትመለሺ ከሆነ ‹የቦርከና ወንዝ› ምልክት ይሁንሽ ማለቱ ነበር።

ይህ ከጥንት የወረስነው "ተራ ምሳሌ" ሊጠቀስ ያስፈለገበት ዋና ምክንያት "እንደ ብርቅ እያየነው ያለው የእለት እንጀራ ፍላጎታችን ቋፍና ጫፍ ላይ ደርሶ ‹መኖር ወይ አለመኖር›" ወደሚለው ውሳኔ ላይ ዜጎች ከመድረሳቸው አስቀድሞ ወፈፌው ኢኮኖሚያች ቢያንስ እብደቱ እንዲበርድለት ክንዶችና እግሮቹ በብረት ሰንሰለት ታብተው አደብ እንዲገዛልን ማድረጉ ውዴታ ሳይሆን ግዴታ ላይ የተደረሰ ይመስለናል። ሆዱ ባዶ ሆኖ ሆድ የባሰው ሕዝብ ርሃቡን ለማሰማት አደባባይ መዋል ከጀመረ ቁጣውን ማስታገስ ስለሚያስቸግር ከወዲሁ ቢታሰብበት አይከፋም። ለመንግሥታችንና ለዘርፉ ተዋንያን የምናስተላልፈው መልእክትም "ልብ ያለው ልብ ያድርግ" የሚለውን የተውሶ አባባል ይሆናል።

**ደፈር ብለን እንዋቀስ!**

እስከ ዛሬ ድረስ ደፈርና ጫን ብለን ለመኼስ "ፈራ ተባ" ስንል የቆየንበትን አንድ መሠረታዊ ጉዳይ እናንሳ። "እባጩን ጫን ብለን ከመዳሰሳችን" አስቀድሞ ግን አንዳንድ መሠረታዊ ጉዳዮችን በመጠቃቀስ ለትዝብታችን መደላደል የሚሆኑ ሃሳቦችን እንጎዝጉዝ። ሀገራዊው ስታትስቲክስ እንደሚነግረን ለመቶ ፐርሰንት ጥቂት ሸርፍራፊ አሀዞች ሲቀሩ የሀገሪቱ ዜጎች በሙሉ በተለያዩ የሃይማኖት ጥላ ሥር የተሰባሰቡ ናቸው።

ጥቅል ፍረጃ ሆኖ እንዳይቆጠር ሰጋን እንጂ በኢትዮጵያ ምድር በአሁኑ ወቅት "ሃይማኖት የለኝም" የሚሉ ቡድኖች ስለመኖራቸው እርግጠኛ መሆን አይቻልም። በየከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚገኙ አንዳንድ የዲያሌክቲክስ ፍልስፍና አስተማሪዎችም ቢሆኑ ደፍረው "አምላክ የለሽነታቸውን" በግላጭ የሚያውጁ አይደሉም። ስለዚህም ነው እያንዳንዱ ዜጋ "የእኔ" የሚለው ሃይማኖት ባለቤት ነው ለማለት የተደፈረው።

እያንዳንዱ ቤተእምነት የሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ለአንድ ደቂቃም ቢሆን ሲያስተጓጉል ያለመታየቱም የየሃይማኖቶቹ ጥንካሬ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። በየአብያተ ክርስቲያናቱ ጉልላት ላይ ከፍ ብለው የተሰቀሉት ድምጽ ማጉያዎች ለፈጣሪ የማያቋርጥ ምሥጋና ሲያቀርቡ ማድመጥ ነፍስን በሃሴት ያረሰርሳል። "አላሁ ከበር!" በሚል አዋጅ በየመስጊዶቹ የሚደመጠው አዛንም የፈጣሪን ታላቅነት አጉልቶ ለማሳየት የሚተላለፍ ዘወትራዊ የማንቂያ ታላቅ መልእክት ነው። የወንጌል አማኞች "የሃሌሉያ ዝማሬም" ከአማንያኑ አንደበት አልጎደለም። የባህላዊ እምነት ተከታዮችም ቢሆኑ በአምልኮታዊ ሥርዓታቸው መሠረት ፈጣሪያቸውን የሚያመሰግኑት በመስጠት ነው። ለጊዜው ከድምጽ ከፍታና ዝቅታ ጋር ተያይዞ የሚነሳውን "የዴሲቢሉን" ፍተሻ ጣጣ ቦታው ስላይደለ አንነካካውም።

እንደየእምነቶቹ ቀኖናና ሥርዓት መሠረት ምእመናን በሚሰበሰቡባቸው ጉባኤዎችም የየሃይማኖት መምህራን አባላቶቻቸውን ስለ ቀኖናና ትውፊታቸው የሚያስተምሯቸው ከልባቸውና ለእምነታቸው ቀናዒ ሆነው ነው። የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት አንጻራዊም ቢሆን፤ ትልቁ ጥንካሬያቸው በራሳቸው ዶግማና ትምህርት ብርቱ መሆናቸው ብቻም ሳይሆን አንዱ የእምነት ክፍል ከሌላኛው ጋር ተከባብሮ መኖራቸው ድንቅና አስመስጋኝ የጋራ እሴታቸው ነው።

ይህ መሠረታዊ አቋማቸውና የእምነታቸው አስተምህሮ እንደተጠበቀ ሆኖ ግራ እያጋቡን ያሉ የጋራ ጉዳዮች መኖራቸውንም መካድ አይቻልም። ዛሬ ሀገሪቱ በፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚው ወይንም በሌሎች ማሕበራዊ ጉዳዮች እንዳትረጋጋ ምክንያትና ሰበብ በመሆን ጦርነት፣ ውድመትና ክፋት ቆስቋሽና አስፈጻሚ ሆነው የምናያቸው የጥፋት መልእክተኞች በሙሉ በሀገሪቱ ካሉት የሃይማኖት ተቋማት መካከል በአንደኛው ሥር የተጠለልን ነን ማለታቸው አይቀርም።

በንግዱ ሥርዓት ውስጥም ቢሆን ባልተገባ መንገድ ሲስተሙን የሚበክሉ፣ በግፍ ተግባር ተክነው ባእድና ገዳይ ቁሶችን ወገኖቻቸው ከሚመገቡት ምግብ ጋር ቀላቅለው የሚሸጡ መኖራቸው የአደባባይ ምሥጢር ከሆነ ውሎ አድሯል። የሕዝብን መሬትና ሀብት ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱን ሉዓላዊ ክብር ለመሸጥና ለመለወጥ ሌት ተቀን የሚያደቡትም ቢሆኑ "ሃይማኖታችሁ ምንድን ነው?" ተብለው ቢጠየቁ ወደ አንዱ የእምነት ጎራ ጣታቸውን መጠቆማቸው አይቀርም።

በጉቦ፣ በዘረፋ፣ በቢሮክራሲውና በፖለቲካ ቡድናቸው ታዛ ስር ተጠልለውና ተሸሽገው ባለጉዳዮችን በማጉላላትና በማስለቀስ የተካኑትም ቢሆኑ ነፍሳቸውና ሥጋቸው መበከሉን እያወቁ እንኳን "የየትኛው ሃይማኖት ተከታዮች ናችሁ?" ተብለው ቢሞገቱ እንደተለመደው "የእከሌ ነና!" ብለው ማረጋገጫ መስጠታቸው ብቻም ሳይሆን በውጭ መገለጫቸውና በቋንቋቸው ጭምር በእምነታቸው እንደሚኩራሩ ለመመስከር የሚያቅማሙ አይደሉም። እንደዚህ የዘረፋውንና የውንብድናውን ወዘተ. ፈጻሚና አስፈጻሚዎች በየፈረጃቸው እየዘረዘርን እንፈትሽ ብንል እያንዳንዱ ተዋናይ በእርግጠኛነት "የአንደኛው ሃይማኖት ተከታይ ነኝ" ማለቱ አይቀሬ ነው።

እነዚህን የመሳሰሉ ሀገራዊ ህፀጾቻችንን ለማረቅና ምእመኑን ከመሰል ድርጊቶች ለመመለስ የየሃይማኖቶቻችን የትምህርት ጉልበቶች ስለምን አቅም አጥተው ተልፈሰፈሱ ብለን ብንሞግት ሊያስወቅሰን አይገባም። የሃይማኖት አስተማሪዎች ለሰማያዊው ጽድቅ ብቻ ሳይሆን በምድራዊው ኑራችንም እረፍት እዲኖረን ጠንክረው ለመስራት ስለምን አቃታቸውው? በትምህርቶቻቸው ፍሬስ ከዕለት ወደ ዕለት እየከፋ የሚሄደው ኑሯችን ስለምን ሊፈወስ አልቻለም። ፆሙና ጸሎቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ምነውሳ የምእመናን የሕይወት ለውጥ እንደ ሰማይ ሊርቅብን ቻለ?

ኢሥነምግባራዊ በሆነ መልኩ አንዱ በሌላው ላይ ለመጠፋፋት እንዲነሳሳ ክፉ ዘር ሲዘሩ ውለው የሚያድሩት የክፋት መገለጫ ዜጎች "ሃይማኖቴ!" የሚሉት መሸሸጊያ እንዳላቸው የሚያጠያይቅ እንዳልሆነ የተግባባን ይመስለናል። "ከመልካም ተግባር የተፋታ ሃይማኖት የሞተ ስለመሆኑም" መምህራኑ "ሰዎቻቸውን" ስለምን በሥልጣነ "ክህነታቸው" እየገሰጹ እንደማያርሟቸው ግራ ያጋባል። እነዚህን መሰል በሃይማኖት "አርቲፊሻል የወርቅ ቀለም የደመቁ" ዜጎች አንድም በቋንቋቸው አለያም "ሃይማኖተኛ" ስለመሆናቸው በበርካታ ጠቋሚ ምልክቶች በቀላሉ የሚለዩ ሆነው እያለ ቸል መባላቸው ወይንም ለመንግሥት ውሳኔ ብቻ መተዋቸው ምክንያቱ ሊገባን አልቻለም። የሃይማኖት አባቶች መክረውና ዘክረው ሲታክታቸው "ያወግዛሉ" የሚባለው "እውነትስ" ምነው አዚም ሸፍኖት ደበዘዘብን?"

ከጥቂት ቀናት በፊት ይህ ጸሐፊ በተገኘበት አንድ ሃይማኖታዊ ጉባዔ ላይ የዕለቱ መምህር ትኩረት ሰጥተው ለምእመኑ ያስተላለፉት ትምህርት በበጎ አርአያነት የሚያስመሰግን ነበር። "አንዳንዶቻችሁ..." ብለው ጀመሩ መምህሩ። "ከዚህ ጉባኤ ውስጥ አንዳንዶቻችሁ ከድሃ ላይ በግፍ እየዘረፋችሁ ከምትሰበስቡት ገንዘብ አሥራት፣ መባ፣ በኩራት ወዘተ. እያላችሁ ለእግዚሃር ቤት አገልግሎት የምትሰጡት ስጦታ ተገቢ ስላልሆነ ረክሳችሁ የፈጣሪን ቤት አታርክሱ። በግፍ የሚገኘውን ገንዘባችሁን በላብ ዋጋ ከተሰበሰበው የምእመናን ገንዘብ ጋር አትቀላቅሉ። "

"ፍትህን የምታጓድሉ፣ መደበኛ ተግባራችሁን ስትከውኑ ተገልጋይ የምታስለቅሱ፣ በንግዳችሁ እያጭበረበራችሁ ክብረትን የምትናፍቁ እንደ ጅማሬያችሁ ፍጻሜያችሁ ስለማያምር ቀኑ ሳይመሽባችሁ ፈጣሪ አምላካችሁ ኑና እንዋቀስ እያለ ጥሪ በማቅረብ ይጋብዛችኋል። በበደላችሁና በግፋችሁ የምትቀጥሉ ከሆነ ግን የምትመኩበት ሁሉ እንደ ጉም ይበናል፤ እንደ ትቢያም ከንቱ ይሆናል። ሳይመሽ በተሰጣችሁ ዕድል ንሰሃ ገብታችሁ ተመለሱ። "

ከቤተ እምነቶቻችንና ከየምስባኮቻችን የጎደለብን ይህን መሰል ጠንክር ያለና ለንሰሃ የሚያደፋፍር ትምህርት ይመስለናል። ለጊዜው ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚኖራቸውን ሚና በተመለከተ በሌላ ጊዜ እንመለስበታለን። በዚህ ጽሑፍ በዋነኛነት ለማስተላለፍ የተሞከረው መልእክት የሃይማኖት መምህራኖቻችን በትምህርቶቻቸው እያነጹ እኛን ምእመናን ያርቁ የሚል ነው። ይህ እስካልሆነ ድረስ ሀገራችን ከገባችበት አረንቋ ፈጥና ልትወጣ ትችላለች ማለት ዘበት ነው። ታዲያ ማን ከማን ይዋቀስና ንሰሃ ይግባ? ለሚለው ጥያቄ መልሱ በቀዳሚነት ከህሊናችን ጋር፣ ቀጥሎም ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚመክረን ከፈጣሪ ጋር ሊሆን ይገባል። ሰላም ይሁን!

# ለካፒታል ገበያው ውጤታማነት የተጀመረው ቀዳሚ የቤት ሥራ

**ፍሬሕይወት አወቀ**



**ከፋይናንስ ተቋማት ለተውጣጡ ባለሙያዎች የመጀመሪያው ሥልጠና በተሰጠበት ወቅት**

ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ በአገሪቱ የመጣውን ለውጥ ተከትሎ የተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ውጤቶች ተመዝግበዋል። በተለይም በኢኮኖሚ ላይ ለውጥ ማምጣት የሚያስችሉ የሪፎርም ሥራዎች ሲካሄዱ ቆይተዋል። ከዚህ አኳያም አንዱ የሚጠቀሰው የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው ነው።

በፋይናንስ ዘርፍ ላይም እንዲሁ የሪፎርም ሥራዎች እየተካሄዱ ይገኛሉ። በሀገሪቱ ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ እየተደረገ ያለው የካፒታል ገበያና የውጭ ባንኮች በሀገሪቱ የሚሰሩበት ሁኔታ መመቻቸቱም በዘርፉ የተካሄዱ ማሻሻያዎችን ተከትሎ በሀገራችን ሊተገበሩ የተቃረቡ ስራዎች ናቸው።

በአክሲዮን ገበያ አስፈላጊነት ላይ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ፋይዳውን በመዘርዘር ምክረ ሃሳቦችን ሲሰጡ ኖረዋል። የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች፤ በሀገሪቱ የካፒታል ገበያ የካፒታል ምንጭ በመሆን እንደሚያገለግል ይናገራሉ። የንግድ ድርጅት ለማቋቋም ወይም የተቋቋመ ድርጅትን ለማስፋፋት ሲያስፈልግ፣ የመጀመሪያው ጥያቄ ድርጅቱን ለማቋቋም ወይም ለማስፋፋት የሚያስፈልገው ካፒታል ከየትና እንዴት ይገኛል የሚል ጥያቄ ይነሳል የሚሉት ባለሙያዎቹ፣ ባህብቶች መሠረተ ሰፊ የንግድ ድርጅቶችን ለማቋቋምና ለማስፋፋት በፈለጉ ጊዜ ከፍተኛ ካፒታል ለማሰባሰብ በበርካታ አገሮች ዘንድ የታወቀውና የተለመደው መንገድ የአክሲዮን ወይም ወደ ገንዘብ የሚቀየሩ ሰነዶች ገበያ እንደሆነ ያብራራሉ።

የአክሲዮን ገበያው ምንነትና ጥቅም ላይ ግንዛቤ ባለው ሕብረተሰብ ውስጥ የገበያው መሠረት ሕዝቡ እንደሚሆንም ነው የተጠቀሱት። ግብይቱ የማይነጥፍ የካፒታል ምንጭ በመሆን የሚጫወተው ሚና ትልቅ እንደሆነም ያስረዳሉ። የአክሲዮን ገበያ ሌላኛው ጠቀሜታ የኢንቨስትመንት አማራጭ መሆኑና የቁጠባ ባህልን ለማዳበር ማስቻሉ መሆኑንም ያመለክታሉ። ሕዝብ አሳታፊ መሆኑ ተመራጭ ያደርገዋል።

የአክሲዮን ገበያ በአንድ ኩባንያ ውስጥ አክሲዮን በመግዛት የኩባንያው የጋራ ባለሀብት ለመሆን ብሎም ከሚያስገኘው ትርፍ ተጠቃሚ ለመሆን ለሚፈልጉ ሁሉ ክፍት መሆኑን በመጥቀስም፣ ሁሉም እንዳቅሙ አክሲዮን እየገዛ የንግድ ድርጅት ባለንብረት እንዲሆን ያስችላል ይላሉ። ስለዚህ ጥቂት ከበርቴዎች ብቻ ኢኮኖሚውን እንዳይቆጣጠሩ ከመከላከሉም በላይ የሀብት ሥርጭትን እንደሚያሰፋ ጠቅሰው፣ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች መንግሥት የካፒታል ገበያው እንዲጀመር የጊዜ ሰሌዳ አስቀምጦ እየሠራ መሆኑን በመልካም ጅምር ይጠቅሳሉ።

ኢኮኖሚውን ለመደገፍ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል፤ በርካታ ዕድሎችንም ይከፍታል፤ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትም የጎላ አበርክቶ ይኖረዋል ተብሎ ትልቅ ግምት የተሰጠው የአክሲዮን ገበያን ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በመንግሥትና በግል ድርጅቶች አማካኝነት እየተሠሩ ይገኛሉ።

ይህ ተቋማዊ ሥርዓት የሚያስፈልገውና ሕዝብ የሚተማመንበት የገበያ ሥርዓትን የሚጠይቀው የአክሲዮን ገበያ በርካታ አገራት ኢኮኖሚያቸውን ከፍ ያደረጉበት ቢሆንም፣ ጥቂቶች ደግሞ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን ባለማሟላታቸው ሳቢያ ውጤታማ ሳያደርጋቸው እንደቀረ መረጃዎች ያመለክታሉ።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ እንደ አሜሪካ፣ እንግሊዝና ካናዳ በመሳሰሉ አገራት የካፒታል /የአክሲዮን/ ገበያው የተለያዩ ኢንቨስትመንቶችን በማስፋፋት ለአኮኖሚያቸው አጋዥ ሞተር ሆኖ አገልግሏል። ታዲያ የአክሲዮን ገበያን ተግባራዊ ለማድረግ እየተሰናዳች ያለችው ኢትዮጵያም ከሌሎች አገራት ልምድ በመውሰድ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎቿን ከወዲሁ አጠናክራ መሥራት እንዳለባት ባለሙያዎች እየመከሩ ይገኛሉ።

ኢትዮጵያ ወደ ካፒታል ገበያ ለመግባት እጅግ በመዘግየቷ ያጣቻቸው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ቢኖሩም፤ በተመሳሳይ ደግሞ ቀድመው ተግባራዊ ካደረጉና ከፍተኛ ልምድ ካካበቱ አገራት ልምድ በመውሰድ ውጤታማ መሆን የምትችልበት አጋጣሚ ስለመኖሩ በማንሳት ዕድሉን በጥንቃቄ መጠቀም እንደሚገባ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህር ዶክተር ሞላ አለማየሁ፤ የአክሲዮን ገበያ ሲመሰረት ሰፋፊ መሰረተ ልማቶች የሚያስፈልጉት እንደሆነ በማንሳት መሠረተ ልማቱም ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ እንደሚጠይቅ ያስገነዝባሉ። እንደሳቸው ገለጻ፤ ከመገበያያው ሕንፃ ጀምሮ አስፈላጊ የሆኑ የቢሮና የመረጃ ቁሳቁስ ማሟላት፣ የጥበቃና ደህንነት ግብዓቶች፣ ዘመኑ የደረሰበትን ዕድገት የሚመጥን የመረጃ መረብ መዘርጋትና ለዚህ ሥራ ብቁ የሆነ የሰው ኃይል ማፍራት ያስፈልጋል።

ዶክተር ሞላ ስቶክ ማርኬት ወይም የአክሲዮን ገበያ ለኢኮኖሚው ዘርፍ የሚኖረው ጠቀሜታ የጎላ መሆኑን በመጥቀስም አጠቃላይ ሊገጥመው ይችላል ያሉትን ችግርና መወሰድ ስለሚገባው ጥንቃቄ አስረድተዋል። የአክሲዮን ገበያ በኢትዮጵያ እንዲጀመር ከፍተኛ ግፊት ሲደረግና ብዙ ሲባልለት የነበረ መሆኑን አስታውሰው፣ በተለይም የካፒታል ማርኬቱን የሚያሳልጥ ስለመሆኑ ያላቸውን እምነት ያመለክታሉ።

‹‹የአክሲዮን ገበያ በዋናነት ከፍተኛ የካፒታል አቅም በመፍጠር ለግሉ ዘርፍ ምጣኔ ሀብት የገንዘብ ፍሰትን የሚያሻሽል፣ በቀላሉ ወደ ገንዘብ ሊለወጥ የሚችል ሀብትን መፍጠር የሚችልና ባለሀብቱና ባለድርሻው ትርፍም ሆነ ኪሳራቸውን በጋራ እንዲጋሩ የሚያስችል ሥርዓት እንደመሆኑ በኢኮኖሚው ላይ በጎ ተጽእኖ ያመጣል›› የሚሉት ዶክተር ሞላ፤ ከፍተኛ ግምት የተሰጠውን ይህን የአክሲዮን ገበያ በኢትዮጵያ ተግባራዊ ለማድረግ በርካታ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መከናወን እንዳለባቸው ነው ያሳሰቡት።

የአክሲዮን ገበያ ከመፈጠሩ አስቀድሞ ጠንካራ ተቋማትን መገንባት የግድ እንደሆነ በማንሳት በተለይም በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል በማብቃት ረገድ ለአብነትም ኦዲተሮችን፣ የሂሳብ ባለሙያዎችን፣ የስቶክ ብሮከሮችንና የአክሲዮን ጠበቆችን ማሰልጠን የሚችሉ ጠንካራ ተቋማትን መገንባት ቀዳሚ ሥራ መሆኑ ይታመናል።

ይህንኑ ለማሟላትም እንቅስቃሴ እያደረገ የሚገኘው አይ ካፒታል አፍሪካ ኢንስቲትዩት ተጠቃሽ ነው።

ኢንስቲትዩቱ ከሰሞኑ ከናይሮቢ ሴክዩሪቲስ ኤክስቼንጅ ጋር በመተባባር ለአክሲዮን ገበያው ውጤታማነት የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን እየሠራ እንደሆነ ተገልጿል። የአይ ካፒታል አፍሪካ ኢንስቲትዩት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶ/ር ገመቹ ዋቅቶላ ጉዳዩን አስመልክቶ በተዘጋጀ መድረክ ላይ የካፒታል ገበያ በኢትዮጵያ መጀመሩ ብቻ ሳይሆን እንዴት ውጤታማ ሊሆን ይችላል? የዘርፉ ተዋናዮችስ እነማን ናቸው? የሚለውን መለየትና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

በሌሎች አገራት ተሞክሮ የአክሲዮን ገበያ ውጤታማ የሆነባቸው አራት መሰረታዊ ነገሮች ስለመኖራቸው የጠቀሱት ዶ/ር ዋቅቶላ፣ ከእነዚህ አራት መሰረታዊ ነገሮች መካከልም ኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኞቹ እየተሠሩ እንደሆነ ነው ያመለከቱት። አንደኛው የመሰረተ ልማት ግንባታ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህ መሰረተ ልማት በሚገባ መልማት እንዳለበት አንስተዋል። ሁለተኛው የገበያ ልማት እንደሆነ ተናግረው፣ ይህ ማለት ደግሞ የሚሸጠው ነገር ሲሆን ለአብነትም ቦንድና ሼር መሸጥ መለወጥ የሚችሉት ተጠቃሽ ሲሆኑ ሶስተኛው የፖሊሲና የቁጥጥር ሥርዓቶች ናቸው። እነዚህም እየተሠራባቸው ሲሆን፤ አራተኛውና ቁልፍ ጉዳይ የአቅም ግንባታ እንደሆነም ያብራራሉ። አቅም ግንባታ ሁለት መሰረታዊ ነገሮችን የሚይዝ እንደሆነ በመግለጽ አንደኛው የሰው ኃይል ግንባታ፣ ሁለተኛው ደግሞ ተቋማዊ አቅሞችን መገንባት እንደሆነ አስረድተዋል።

የሰው ኃይል ግንባታና ተቋማዊ አቅሞችን መገንባት ለካፒታል ገበያው ውጤታማነት ቁልፍ ተግባራት እንደሆኑ አስታውቀው፣ ከሌሎች አገራት ልምድ በመውሰድ የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ልማትን ውጤታማ ማድረግ እንደሚቻል ዶ/ር ዋቅቶላ ይጠቁማሉ። ለዚህም ድርጅታቸው አይ ካፒታል አፍሪካ ኢንስቲትዩት ለዘርፉ ቁልፍ ሚና ያላቸውን ሥራዎች እየሠራ እንደሆነም አስረድተዋል። ከሥራዎቹ መካከልም አቅም በመገንባትና ልምድ ካካበቱ በተለይም ጎረቤት ከሆኑ አገራት ጋር በመሆን በተግባር የሚታየውን የአክሲዮን ገበያ ሥራ ወደ ኢትዮጵያ በማምጣት እንዴት እንደሚሠራ ሥልጠና መስጠት የሚለው ይገኝበታል ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የካፒታል ገበያ እንደማንኛውም ሸቀጥ ሻጭና ገዢ ሕግና ሥርዓት ባለው መንገድ ተገናኝተው መገበያየት እንዲችሉ የሚያደርግ ነው፤ በርካታ ጠቀሜታዎችም አሉት። መንግሥት ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቁ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ለመስራት ሲያስብ ገንዘቡን ማግኘት ይቸገራል። በዚህ ጊዜ ሕዝቡ በካፒታል ገበያ ውስጥ ተሳታፊ በመሆን ፕሮጀክቱ ገንዘብ ማመንጨት እንዲችል ይሆናል። ይህ አንድ ፋይዳው ነው። አክሲዮን በመግዛት ትርፍ ማግኘት ማስቻሉ ነው። ሁለተኛው ፋይዳው ደግሞ መንግሥት በእጁ ያሉትን ተቋማት ወደ ግለሰቦች ማዘዋወር ሲፈልግ ወደ ካፒታል ገበያ ማውጣት ያስችለዋል። በዚህ ጊዜ ማንኛውም ሰው ኢንቨስት የማድረግ ዕድል ይኖረዋል።

ይህ የካፒታል ገበያ በትክክል ተግባራዊ እንዲሆን አይ ካፒታል ኢንስቲትዩት በዋናነት አጠቃላይ የገበያው ሲስተም አቅም፣ ዕውቀትና ልምድ ባላቸው አካላት እንዲደገፍ ያመቻቻል። ለዚህም የመንግሥት አካላትን ጨምሮ የፖሊሲ ሰዎችን የዘርፉ ቁልፍ ተዋናይ ለሆኑ ባለሙያዎችና ተቋማት ልምድ ባላቸው አካላት አቅማቸውን መገንባት፣ የምክር ሃሳብ መስጠት፣ የተለያዩ ሥልጠናዎችን መስጠትና ዕድሎችን ማመቻቸት ነው።

የአክሲዮን ገበያን በኢትዮጵያ ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ውስጥ የመጀመሪያ አጋር የሆነው የኬንያው ናይሮቢ ሴክዩሪቲስ ኤክስቼንጅ ሲሆን፤ በዘርፉ ከ70 ዓመት በላይ የዳበረ ልምድ ያለው ነው። ተቋሙ ወደ ኢትዮጵያ ገበያ ገብቶ አዲስ የሚመሰረተውን የአክሲዮን ገበያ የማገዝ ከፍተኛ ፍላጎት ያለው ስለመሆኑም ያስረዱት ዶክተር ዋቅቶላ፤ ጎረቤት አገር ከሆነችውና በዘርፉ ከፍተኛ ልምድ ካካበተችው ኬንያ ጋር በመሥራት ልምዳቸውን በመጠቀም የኢትዮጵያን የካፒታል ገበያ ልማት ውጤታማ ማድረግ እንደሚቻል ነው ያስገነዘቡት።

አይ ካፒታል ኢንስቲትዩት በአክሲዮን ገበያ ከፍተኛ ልምድ ካለው የኬንያ ናይሮቢ ሴክዩሪቲስ ኤክስቼንጅ ጋር በመተባበር ተጨባጭ በሆነ መንገድ የካፒታል ገበያ ልማት ውጤታማ እንዲሆን ይሠራል። የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያን ውጤታማ ለማድረግ ጽኑ ፍላጎት ያላት ኬንያ ከኢትዮጵያ ጋር የሚመሳሰል ማህበረ ኢኮኖሚ ያላት በመሆኑ የተፈጠረው አጋርነት ውጤታማ እንደሚሆን ያላቸውን እምነት በመግለጽ፤ የእነሱ ተሞክሮም የአክሲዮን ገበያው ኢትዮጵያ ውስጥ እንዴት ሊተገበር እንደሚችል፣ አቅም በመገንባትና በጋራ እንዴት መሥራት እንደሚቻል የምክር አገልግሎቶችን ማግኘት ዋናው ጉዳይ ይሆናል ይላሉ።

ሁለቱ ድርጅቶች በገቡት የውል ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ በካፒታል ገበያ ለመሳተፍ ለሚፈልጉ ድርጅቶችና ቡድኖች የማማከርና የሥልጠና አገልግሎቶችን፣ በገበያው አመሰራረት ዙሪያ ለኢትዮጵያ መንግሥት ተሞክሮን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ድጋፎችን እንዲሁም የድርጅቶችን ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠናዎችን በጋራ የሚሰጡም ይሆናል። በአሁኑ ወቅትም ለአክሲዮን ገበያው ዋና ቁልፍ የሆኑ ተዋናዮችን ከተለያዩ ባንኮች በማሰባሰብ የመጀመሪያውን ዙር ሥልጠና በመስጠት የጋራ ሥራቸውን ጀምረዋል።

በመጀመሪያው ዙር የተሰጠው ሥልጠናም የተሳካና ውጤታማ እንደነበር ያነሱት ዶክተር ዋቅቶላ፤ ሥልጠናው ቀጣይነት ያለውና አቅም መፍጠር የሚችል እንደሆነ ተናግረዋል። ከሥልጠናው ባሻገር የካፒታል ገበያን በኢትዮጵያ ውጤታማ ለማድረግ ሁሉም ሰው በአገር ደረጃ ስለጉዳዩ ምንነት መረዳት፣ እንዴት መጠቀምና መሳተፍ እንደሚችል ማወቅ ይኖርበታል። ይህን ማድረግ ሲቻል ካፒታል ገበያን ውጤታማ ማድረግ ይቻላልም ነው የሚሉት።

የናይሮቢ ሴክዩሪቲስ ኤክስቸንጅ ሥራ አስኪያጅ ዴቪድ ዋኔይና ደግሞ፤ በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ምስረታ ቢዘገይም፣ የድርጅታቸውን ልምድና የአገሪቱን የህዝብ ቁጥር በመጠቀም ስኬታማ የካፒታል ገበያ ልማት መመስረት ይቻላል ሲሉ ይገልጻሉ። በስምምነቱ መሰረትም የመጀመሪያ የሆነው፣ ከፋይናንስ ተቋማት ለተውጣጡ ባለሙያዎች በካፒታል ገበያ ባለድርሻዎችና ከገበያው ጋር ተያይዘው ስለሚመጡ የሥራ እድሎች የሁለት ቀናት ሥልጠና በሳፋየር አዲስ ሆቴል የተሰጠ መሆኑን ተናግረዋል። በቀጣይም መሰል ሥልጠናዎች በመስጠት ቀጣይነት ያለውና ውጤታማ የሆነ ግንኙነት እንደሚኖራቸው አስረድተዋል።

አይ ካፒታል አፍሪካ ኢንስቲትዩት ከተመሰረተ ሰባት ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን፤ የምስራቅ አፍሪካ ዓመታዊ የፋይናንስ ጉባኤን ለተከታታይ አምስት ዓመታት በማዘጋጀት ይታወቃል። ከዚህም በተጨማሪ በፋይናንስ ዘርፋም ሆነ ከፋይናንስ ዘርፍ ውጭ የሰው ኃይል ግንባታ ላይ ከፍተኛ ድርሻ ያለው ድርጅት መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የበይነ መረብ ዝርያዎችን ብቻ አትመኑ!

**ዋስልኝ አየለ**

የበይነ መረቡ ዓለም (ኢንተርኔት) ሥራዎችን ሁሉ ያቀለለ፣ መረጃዎችን በቀላሉ እንድናገኝና ለፈለግነው አካልም በቀላሉ እንድናስተላልፍ ያደረገ ነው። በኢንተርኔት አማካኝነት የየራሳቸው አገልግሎት ያላቸው በርካታ ፕላትፎርሞች ተፈጥረዋል። በአጠቃላይ ዓለምን መንደር አድርገዋል። ያም ሆኖ ግን ደካማ ጎኖችም አሏቸው።

እነዚህ ሁሉ የበይነ መረብ አማራጮች ሰነፍ አድርገውናል። በህትመት (hard copy) ያሉ ነገሮችን (መጽሐፍ፣ ጋዜጣ፣ መጽሔት...) እንዳናነብ አስንፈውናል። በበይነ መረብ (soft copy) የሚነበብ ነገር ደግሞ በባህሪው ችኩል ያደርጋል። ጥልቅ እሳቤና ትርጓሜ እያደረግን አናነበውም። ለዚህ ምቹ በህትመት የሚጻፉት ናቸው።

የህትመት ውጤቶችን (መጽሐፍ፣ ጋዜጣ፣ መጽሔት...) ስናነብ የተረጋጋ ቀልብ ይኖረናል። ምክንያቱም ወሰናቸው ይታወቃል። እንኳን ጋዜጣና መጽሔት ብዙ ገጾች ያሉት መጽሐፍ ራሱ ወሰኑ ይታወቃል። ለምሳሌ አንድ ዳጎስ ያለ መጽሐፍ ብናነብ የገጹን ብዛት ቀድመን ነው የምናውቀው። ስለዚህ እስከመጨረሻው እናነበዋለን። ጋዜጣና መጽሔት ደግሞ ከዚህም የቀለሉ ናቸው።

ስለዚህ የህትመት ውጤቶችን ስናነብ የተሰበሰበ ቀልብ ነው የሚኖረን። ሃሳቦቹን እያብሰለሰልን እና እየተረጎምን ነው የምንሄደው። ከተጻፈው ነገር ተነስተን ሌሎች ሃሳቦችን ራሱ እናመነጫለን። ከራሳችን የሕይወት አጋጣሚ ጋር እያመሳጠርን እንሄዳለን።

ወደ በይነ መረቡ ዓለም ስንሄድ ግን ይህ ዕድል የለም። ለምሳሌ በአገራችንም በዓለምም ብዙ ተጠቃሚ ያለውን ፌስቡክን እንውሰድ፤ ረጃጅም ጽሑፍ ስናገኝ ጊዜ ሲኖረኝ አነበዋለሁ ብለን Save እናደርገዋለን፤ ዳሩ ግን አናነበውም። ምክንያቱም ወሰን የለውም፤ በየደቂቃው አዳዲስ ነገር ስላለው ጊዜ ብናገኝም ትዝ ብሎን ወዳስቀመጥንበት ቋት ሄደን አናነበውም። በየደቂቃው የሚፈጠረውን ነገር ለማየት ነው ቀልባችን የሚንጠለጠል። ወደታችም ወደ ላይም በወረድን (Scroll) ባደረግን ቁጥር አዳዲስ ነገር ስላለ የሩጫ ንባብ ነው የሚሆን።

ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ትልቁ ስጋት የኢንተርኔት ዓለም በሆነ ቴክኒካል ችግር ለአንድ ቀን ቢሰናከል (Fail ቢያደርግስ?) የሚለው ነው።

ይህን ያሳሰበኝ ባለፈው ሳምንት ብዙ ሰዎች ተከታይ (Follower) ቀነሰብን ሲሉ ስለነበር ነው። ካምፓኒው ቴክኒካል ችግር አጋጥሞት መሆኑን አሳውቋል። ወዲያውኑ ስለተስተካከለ ለጊዜው ይሄ ቀላሉ ችግር ነው።

ዳሩ ግን የነበሩ መረጃዎችን ሁሉ የሚያጠፋ ቴክኒካል ችግር ቢያጋጥምስ? እንዲህ አይነት ችግር በሌሎችም የበይነ መረብ ፕላትፎርሞችም ተከስቶ ቢሆንስ? በቀጣይ ደግሞ ከዚህ የባሰ ችግር ቢያጋጥምስ?

ልብ ብላችሁ ከሆነ የሆነ ነገር Youtube ላይ አይተን፤ ከሆነ ጊዜ በኋላ ስንፈልገው ላናገኘው እንችላለን። ለጊዜው የቻናሉ አስተዳዳሪዎች ስለሚያነሱት ይሆናል፤ አጠቃላይ ካምፓኒው ቴክኒካል ችግር ቢያጋጥመው ግን ሁሉም ሊጠፉ ይችላሉ ማለት ነው።

መረጃ ስልክ ላይ ብቻ አታስቀምጡ (ስልኩ ቢጠፋ እንኳን) እንደሚባለው ሁሉ በኢንተርኔት አማራጮች ብቻ መወሰንም አያስተማምንም። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ደግሞ የተጠናወተን ልማድ የበይነ መረብ መረጃዎች ላይ ጥገኛ መሆን ነው። ሰነዶችን እዚያው ላይ ማስቀመጥ ነው። ስልክ ቢጠፋ እንኳን ይገኛሉ በሚል በበይነ መረብ የግል አካውንቶቻችን የመረጃ ቋት እናስቀምጣለን። ይህ ጥሩ ነገር ቢሆንም ዳሩ ግን የበይነ መረቡ ዓለምም ችግር ሊያጋጥመው ይችላል።

እርግጥ ነው በህትመት ደረጃ ያለ ነገርም አደጋ ያጋጥመዋል፤ ይህ የታወቀ ነው። እዚያ ድረስ እናስብ ከተባለማ አያድርገው እንጂ የሰው ልጅን የሚያጠፋ አደገኛ ወረርሽኝም ሊከሰት ይችላል።

መረጃን ለመሰነድም ሆነ ለጥልቅ ንባብ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው የህትመቱ ዓለም ትኩረት እያጣ ነው። የሚገርመው ግን ይህ የሆነው የረቀቀ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ አገራት ከሆኑት ይልቅ በእኛ በታዳጊ አገራት መሆኑ ነው። በአውሮፓ አገራትና በአሜሪካ ዛሬም ተፅዕኖ ፈጣሪዎች የህትመት መገናኛ ብዙኃን ናቸው። ጎረቤታችን ኬንያ እንኳን የጎበኟት ሰዎች ሲያወሩ በየመገልገያ ቦታው ጠዋት ጠዋት ጋዜጣ አንባቢ ነው ያለው። እነዚህ አገራት እኛ የምንጠቀማቸውን የበይነ መረብ አማራጮች ተደራሽ ስላልሆኑ ይሆን?

የረቀቀ ቴክኖሎጂ በሚጠቀሙ የአውሮፓና አሜሪካ አገራት የምርመራ ዘገባ የሚሰራው በህትመት መገናኛ ብዙኃን ነው። በዝነኛው ዓለም አቀፍ የፑልቲዘር ሽልማት ዛሬ ድረስ ተሸላሚዎች የህትመት መገናኛ ብዙኃን ጋዜጠኞች ናቸው። ከስፖርት ጋዜጠኞች እንደምንሰማው በትልልቅ ሁነቶች ቅድሚያ የሚሰጠው ለህትመት መገናኛ ብዙኃኑ ነው።

በአገራችን ግን በተቃራኒው ነው፤ ጥቃቅን ሁነቶች ላይ ሁሉ ቅድሚያ የሚሰጠው ለቴሌቭዥን ነው። ለህትመቱ ቅድሚያ ይሰጥ እያልኩ አይደለም፤ ቢያንስ ግን እንደ መገናኛ ብዙኃን እንኳን አለመቆጠሩ እንደ ማህበረሰብም እንደ ምሁራንም ያለንበት ደረጃ ስለሚገርመኝ ነው።

የህትመት ዘርፉ ሰራተኞችና አመራሮችም ግን አንድ ልብ ማለት ያለባቸው ነገር አለ። በህትመት መገናኛ ብዙኃን ባህሪ ነው እየሰራን ያለን? የሚለውን መጠየቅ! ጭፍን ባለ ጥላቻ እና በአሉቧልታ ብቻ መንግሥትን ማብጠልጠል ትዝብት ላይ ይጥላል እንጂ ማንንም አያጓጓም። በመንግሥት በኩል ያሉትም የመንግሥት ባለሥልጣናትን ንግግር እና ውዳሴ ብቻ መደራረብ አሰልቺ ነው የሚሆን፤ ትዝብት ላይ ይጥላል።

የምርመራ ዘገባዎች ቢሰሩ፣ በማሕበራዊ ገጾች የሚራገቡ አሉቧልታዎችን የሚያጠሩ ትንታኔዎች ከምንጩ እና በባለሙያ ቢሰሩ፣ ከሰነድ እና ከምሁራን እያጣቀሱ ጥልቅ መጣጥፎች ቢሰሩ... የአንባቢን ቀልብ ወደ ህትመት መገናኛ ብዙኃን ማምጣት ይቻላል።

እነዚህን ልምዶች ካላዳበርን የበይነ መረቡ ዓለም የሆነ አደጋ ቢያጋጥመው ይዞን ገደል ይገባል። ይህን ያልኩት በዚሁ ምክንያት የተቋረጡ የግል የህትመት መገናኛ ብዙኃን ስለማውቅ ነው። በዚህ ዘመን የህትመት ጽሑፍ የሚያነብ የለም ብለው አልሸጥላቸው ብሎ ነው ያቋረጡት። ለንባብ ምርጫ የይዘት ጉዳይ እንዳለ ሆኖ፤ የበይነ መረቡ ዓለም ጫና ግን ቀላል አይደለም።

የዚህ ጉዳቱ ወደፊት የታሪክ ፀሐፊና ተመራማሪ ለሚሆኑት ጭምር ነው። አሁን አሁን ትልልቅ የመንግሥት ተቋማት ሁሉ መረጃዎችን በበይነ መረብ ብቻ የማስቀመጥ ዝንባሌ ይታይባቸዋል። ነገርየው የመዘመን ምልክት ቢሆንም መረጃዎች ግን በወረቀት ሰነድም መቀመጥ ይገባቸዋል። እንዲያውም አስፈሪው ነገር ወደፊት ሁሉም ነገር ከወረቀት ነፃ አገልግሎት እየተባለ ነው። ከወረቀት ነፃ አገልግሎት ሥራን ቀልጣፋና ምቹ ቢያደርግም በበይነ መረቡ ዓለም አደጋ ካጋጠመ ግን መረጃው ሁሉ ገደል ገባ ማለት ነው። የወረቀትም አደጋ እንደሚያጋጥመው ይታወቃል፤ ቢሆንም ግን በሁለቱም መኖሩ አማራጭ ይሆናል ማለት ነው።

በነገራችን ላይ ትልልቅ ሰዎች (በዕድሜም በዕውቀትም) ከበይነ መረብ ንባብ ይልቅ የወረቀት ንባብን ይመርጣሉ። ምክንያቱም በተመስጦ እና ሃሳቡን እየተነተኑ ማንበብ ነው የሚፈልጉት። እርግጥ ነው ይህን በበይነ መረብ ጽሁፎችም ማድረግ ይቻላል፤ ግን ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በይነ መረብ በባህሪው ቀልብን የማንጠልጠልና የመሮጥ ባህሪ አለው።

ስለዚህ ለማንበብም ይሁን መረጃዎችን ለመሰነድ የህትመት ውጤቶችንም እንጠቀም!

# ዓለም አቀፍ

## በኢራን ማረሚያ ቤት በተከሰተ የእሳት ቃጠሎ በርካታ ሰዎች ጉዳት ደረሰባቸው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢቪን በተባለው የኢራን ማረሚያ ቤት በተከሰተው የእሳት ቃጠሎ በርካታ ሰዎች መጎዳታቸውንና የሟቾች ቁጥርም ስምንት መድረሱን አልጀዚራ ዘግቧል፡፡

ኢራን ቃጠሎውን “ከማሪሚያ ቤቱ ለማምለጥ የተሞከረ ጥቃት ነው” ብላ የምትገልጸው በኢቪን ማረሚያ ቤት የእሳት ቃጠሎ አራቱ ታራሚዎች መተፈንስ አቅቷአቸው መዲያውኑ ሲሞቱ ቀሪው አራቱ ታራሚዎች ግን በምን ምክንያት እንደሞቱ በግልጽ የተነገረ ነገር የለም፡፡

ሆኖም ግን የቴህራን ባለሥልጣናት አራቱ ታራሚዎች በቃጠሎው ምንክያት ሕይወታቸውን ማጣታቸውን ገልጸው፣ ቀሪው ግን በታራሚዎች መካከል በተፈጠረው ግብግብና እሳቱን ለማጥፋት በተፈጠረው ግርግር ሕይወታቸው እንዳለፈ አመላክተዋል፡፡

በሞት የተለዩት ስምንቱም እስረኞች ከስርቆት ጋር በተያያዙ ወንጀሎች ታስረው እንደነበር የፍትህ አካላት መናገራቸውን ምንም እንኳ ለቤተሰቦቻቸው ቢነገራቸውም የግለሰቦቹን ማንነት ግን እስካሁን ይፋ አለመደረጉን አልጀዚራ በዘገባው አስነብቧል፡፡

ከሟቾቹ በተጨማሪም 70 እስረኞች በሕይወት ሲተርፉ ሌሎች 6 ሰዎች ደግሞ በሆስፒታል ውስጥ ሕክምና እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡ አሁን ላይ በማረሚያው ቤት ያለው ሁኔታ የተረጋጋና መሻሻል ላይ መሆኑ ተገልጿል፡፡

ኢቪን ማረሚያ ቤት በሰብዓዊ መብት ድርጅቶች በእጅጉ የሚወገዝና በአሜሪካን መንግሥት በጥቁር መዝገብ ላይ የሰፈረ አስከፊ የሚባል ማረሚያ ቤት ነው፡፡ ማረሚያ ቤቱ በሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚታወቅ ሲሆን በከባድ ወንጀሎች የተጠረጠሩ የፖለቲከኞች እስረኞችና የደህንነት ሰዎች ጨምሮ ሁለት ዜግነት ያላቸው ዜጎች የሚታጎሩበት ማረሚያ ቤት ነው፡፡

ሆኖም ግን ቅዳሜ የተቀሰቀሰው እሳት የፖለቲካ እስረኞች የታሰሩበትን ክንፍ በቀጥታ አልነካም ሲሉ ጥሪ የተደረገላቸው የአንዳንድ እስረኞች ባለሥልጣናት እና ቤተሰቦች ተናግረዋል።



የአገሪቱ መንግሥት ቴሌቪዥን በእሁድ እለት እንደዘገበው ከሆነ የቃጠሎው መንስኤ ከማረሚያ ቤቱ ለማምለጥ ሲሉ በእስረኞች መካከል ግጭት ተቀስቅሶ ነበር፡፡ ቃጠሎውን አስመልክተው አስተያየታቸውን የሰጡት የብዙ እስረኞች ፊት መጥቆሩና ልባቸው በኀዘን መዋጡን አልጀዚራ በዘገባው ገልጿል፡፡

መንግሥት የሕይወት መጥፋቱን አስመልክቶ የተለያዩ ምክንያት ቢያቀርብም በወቅቱ የተኩስና የፍንዳታ ድምጾች ከፍተኛ እንደ ነበሩ በቀጥታ የቪዲዮ ስርጭቶች መጋለጡ በብዙ መልኩ ጥፋቱን ወደ ቴህራን እንደሚያዞር ተነግሯል፡፡

በዚሁ መሰረት አውሮፓ ህብረት እና አሜሪካ በማረሚያ ቤቱን የተከሰተውን ችግር በቅርበት እየተከታተሉ መሆናቸውን የገለጹ ሲሆን ቴህራን የእስረኞቹን ደህንነት እንድታረጋግጥም አሳስበዋል።

የአውሮፓ ሕብረት የውጭ ፖሊሲ ኃላፊ ጆሴፕ ቦሬል በበኩላቸው “የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን እና የአውሮፓ ህብረት ዜጎችን ጨምሮ ለሁሉም እስረኞች ሕይወት ተጠያቂ የኢራን ባለሥልጣናት ናቸው” በማለት በትዊተር ገፃቸው አማካይነት ማስጠንቀቂያ አዘል መልዕክት አስፍረዋል። በአደጋው ዙሪያ ከኢራን አሳማኝ መረጃ እንደሚጠብቁም ጆሴፕ ቦሬል ተናግረዋል፡፡



## ሩሲያና ዩክሬን ሴት ምርኮኞችን ተለዋወጡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሩሲያ እና ዩክሬን ሴት ምርኮኞችን መለዋወጣቸውን ቢቢሲ ዘገበ፡፡

በዚህም መሰረት ሩስያ 108 ሴት የጦር ምርኮኞችን ለዩክሬን ያስረከበች ሲሆን ዩክሬን በበኩሏ 110 ሩሲያውያንን ለሩሲያ ሰጥታለች።

ከነዚህ መሀል 37 የሚሆኑት ዩክሬናውያን እጃቸውን የሰጡት በግንቦት ወር በማሪዮፖል አዞቭስቶል ብረት ፋብሪካ ከበባ ውስጥ ለሳምንታት በቆዩበት ወቅት ነበር።

ብዙዎቹ ሩሲያዊ ሴት ምርኮኞች ደግሞ በንግድ ጫኝ መርከብ ውስጥ ባሕረተኛ የነበሩ ናቸው።

አንዳንዶቹ ሴት ምርኮኞች በሩሲያ የሚደገፉ የዶንባስ ክልል ተገንጣይ ቡድን አባላት ናቸው።

በማኅበራዊ ሚዲያ የተለቀቁ ምስሎች ለጊዜው በውል ካልታወቀ ቦታ ሴት ምርኮኞቹ አገር አቋራጭ አውቶቡስ ሲሳፈሩ የሚያሳዩ ናቸው። በኋላ ላይ የወጡ ፎቶዎች ደግሞ ምርኮኞቹ በመንግሥት ሥር ባለው ዛፖሬዥያ ደቡብ ዩክሬን ከአውቶቡስ ሲወርዱ ታይተዋል።

የዩክሬን ፕሬዝዳንት የቮላድሚር ዘለንስኪ ረዳት አንድሪይ የርማክ በማኅበራዊ ሚዲያ 108 ሴት የጦር ምርኮኞች መለቀቃቸውን ይፋ አድርገዋል። ከነዚህ ውስጥ አብረው ምርኮኛ የሆኑ እናቶችና ሴት ልጆቻቸው ይገኙበታል ብለዋል።

ከነዚህ ምርኮኞች አሥራ ሁለቱ ብቻ የሠራዊት አባላት እንዳልሆኑም አንደሪያ የርማክ ተናግረዋል። ዴኒስ ፑሽሊን የተባሉ የሩሲያ ባለሥልጣን በበኩላቸው ይህ ሙሉ በሙሉ የሴቶች ብቻ የሆነ የምርኮኞች ልውውጥ በእርግጥም መደረጉን ጠቅሰው ይሁንና ሁለት ዩክሬናውያን ግን በሩሲያ መቆየትን መርጠዋል ብለዋል።

ዴኒስ ፑሽሊን እንደሚሉት በዩክሬን ከተለቀቁት ውስጥ 80 የሚሆኑት ሩሲያውያን መርከበኞች ሲሆኑ 30ዎቹ ብቻ የሠራዊት አባላት ነበሩ ብለዋል።

ሩሲያ በዩክሬን ላይ ‘ልዩ ዘመቻ’ በሚል ወረራ መፈጸም ከጀመረች አሁን ስምንተኛ ወር ሊይዝ ነው።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ረቡዕ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ዋልያዎቹ የቻን ዋንጫ የምድብ ጨዋታቸውን የሚያደርጉባቸው ቀናት ታወቀ

ቦጋለ አበበ

በመጪው ጥር በአልጄሪያ አዘጋጅነት በሚካሄደው የአፍሪካ አገራት ቻምፒዮንሺፕ(ቻን) ዋንጫ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን እንደሚሳተፍ ይታወቃል። ዋልያዎቹ ለሶስተኛ ጊዜ በሚሳተፉበት በዚህ ውድድር በምድብ አንድ ከአዘጋጇ አልጄሪያ፣ ሞዛምቢክና ሊቢያ ጋር የምድብ ጨዋታቸውን እንደሚያደርጉ ቀደም ብለው መደልደላቸው ይታወቃል። ከትናንት በስቲያም ዋልያዎቹ የምድብ ጨዋታዎችን የሚያደርጉበት ቀን እና ሰዓት ይፋ ሆኗል። በዚህም መሰረት ጥር 5 ቀን ምሽት 1 ሰዓት ላይ የመጀመሪያ ጨዋታቸውን ከሞዛምቢክ ጋር የሚያደርጉ ሲሆን፣ ጥር 9 - ምሽት 4 ሰዓት ከአልጄርያ ጋር ሁለተኛውን ጨዋታ ያከናውናሉ። ቀሪውን አንድ የምድብ ጨዋታም ጥር 13- ምሽት 4 ሰዓት ከሊቢያ ጋር እንደሚጫወቱ ከወጣው መርሃግብር ለመረዳት ተችሏል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የቻን ዋንጫን ጨምሮ በቀጣይ ወራት ለሚያደርጋቸው አህጉራዊ ውድድሮች ይረዳው ዘንድ ከወዲሁ የወዳጅነት ጨዋታዎችን እየፈለገ እንደሚገኝ ተጠቁሟል። በዚህም በአሰልጣኝ ውበቱ አባተ የሚመራው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የወዳጅነት ጨዋታዎችን ለማድረግ ከአፍሪካ ይልቅ ፊቱን ወደ አውሮፓ በማዞር በሰሜን ምዕራብ አውሮፓ አትላንቲክ ውቅያኖስ ላይ ከምትገኘው ከአየርላንድ ብሔራዊ ቡድን ጋር ለመጫወት የኢትዮጵያ እግርኳስ ፌደሬሽን ጥያቄ እንዳቀረበ ሰሞኑን የወጡ መረጃዎች ጠቁመዋል።

ዋልያዎቹ እኤአ ከ2013ቱ የደቡብ አፍሪካ የቻን ዋንጫ ጀምሮ በአሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው እየተመሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ተሳታፊ መሆናቸው የሚታወስ ሲሆን በቀጣይም በአሰልጣኝ ዮሐንስ ሳህሌ እየተመሩ ለሁለተኛ ጊዜ በመድረኩ ተሳታፊ እንደነበሩ ይታወቃል። ይሁን እንጂ በሁለቱም ተሳትፏቸው ከምድብ ማለፍ ሳይችሉ ደካማ ውጤት በማስመዝገብ ነበር ከውድድሩ የተሰናበቱት። ዘንድሮ ደቡብ ሱዳንን በደርሶመልስ ጨዋታ ውጤት 5ለ0 እንዲሁም ርዋንዳን 1 ለ 0 በማሸነፍ ለሶስተኛ ዋልያዎቹን ለቻን ያበቁት አሰልጣኝ ውበቱ አባተ ካለፉት ሁለት ተሳትፎዎች የተሻለ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ይጠበቃል። አሰልጣኙ ባለፈው ወር ከዋልያዎቹ ጋር ለመቀጠል የሁለት አመት ኮንትራት ሲሰጣቸውም ቡድኑን በዘንድሮው የቻን ዋንጫ ከምድብ ጨዋታ የማሳለፍ ሃላፊነት እንደተሰጣቸው ይታወሳል።



ዋልያዎቹ በመጀመሪያው የቻን የምድብ ጨዋታ ጥር 5 ቀን ሞዛምቢክን ይገጥማሉ፣

በአልጄሪያ አስተናጋጅነት በጥር ወር 2015 ዓ.ም በሚካሄደው ሰባተኛው የቻን ዋንጫ የተሳታፊ አገራትን ቁጥር በመጨመር ከዚህ ቀደም በቻምፒዮናው የሚሳተፉ 16 አገራትን ወደ 18 ማሳደጉን የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) ከወር በፊት አሳውቋል።

በአገር ውስጥ ሊጎች ብቻ የሚጫወቱ ተጫዋቾች የራሳቸው የአፍሪካ ዋንጫ ሊኖራቸው እንደሚገባ በማመን የአፍሪካ አገራት ቻምፒዮና (ቻን) የሚባለውን ውድድር እንደ ዋናው የአፍሪካ ዋንጫ በየሁለት ዓመቱ ማዘጋጀት ከጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል። ዘንድሮ በሚካሄደው ውድድር አስራ ስምንቱ ተሳታፊ አገራት በአምስት ምድብ ተከፍለው የሚጫወቱ ይሆናል።

አስራ ስምንቱ አገራት በሚሳተፉበት የቻን ውድድር አዲስ ይዘት ከአምስቱ ምድብ በሦስቱ ምድቦች አራት አራት አገራት የሚፋለሙ ሲሆን፣ በሁለቱ ቀሪ ምድቦች ሦስት ሦስት አገራት የሚፋለሙ ይሆናል። በአዲሱ የውድድር ሕግ መሰረትም አራት አራት አገራት ከሚፋለሙበት የመጀመሪያ ምድብ ሁለት ሁለት አገራት ወደ ሩብ ፍጻሜ ሲያልፉ ሦስት ሦስት አገራት ከሚፋለሙበት ሁለቱ ምድብ አንድ አንድ አገር ብቻ ቀጣዩን ዙር ይቀላቀላል።

የውድድሩ ሃሳብ ከአስራ አምስት ዓመት በፊት በካፍ የተጠነሰሰ ሲሆን እኤአ 2009 ላይ የመጀመሪያው ውድድር በኮትዲቯር አስተናጋጅነት መካሄዱ ይታወቃል። የመጀመሪያው ውድድር በስምንት አገራት መካከል ቢካሄድም የተለያዩ የአፍሪካ አገራት የመሳተፍ ፍላጎታቸው በመጨመሩ በሁለተኛው ውድድር በቀጥታ ወደ አስራ ስድስት ሊያድግ ችሏል። ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎና ሞሮኮ ይህን ዋንጫ ሁለት ሁለት ጊዜ በማንሳት ስኬታማ ሆነው የሚጠቀሱ ሲሆን ሊቢያና ቱኒዚያ አንድ አንድ ጊዜ የዋንጫው ባለቤት በመሆን ታሪክ አላቸው።

በአልጄሪያ የሚካሄደው የቻን ዋንጫ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ቀድሞ ሊካሄድ ከነበረበት ጊዜ ተራዝሞ የሚካሄድ ሲሆን፣ አልጄሪያ ውድድሩን ለማስተናገድ በይፋ ኃላፊነቱን የወሰደችው በ2018 እንደነበር ይታወሳል። ሰሜን አፍሪካዊቷ አገር አልጄሪያ ይህን በአፍሪካ ሁለተኛውን ትልቅ የእግር ኳስ ውድድር በአራት የተለያዩ ስቴድየሞቿ ለማስተናገድ ዝግጅቷን ከጀመረች ቆይታለች።

ውድድሩን የሚያስተናግዱት ስቴድየሞችም በመዲናዋ አልጄርስ፣ በኦራን ከተማ የሚገኘው ኦሊምፒክ ስቴድየም፣ በአናባ የሚገኘው ቻሂድ እንዲሁም በሃምሎዩ የሚገኘው ኮንስታንቲን ስቴድየሞች ውድድሩን ለማስተናገድ ተመርጠዋል።

## ከኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# እኛው የእኛው አቅም፤ እኛው የእኛው ብርታት

**አሸናፊ መስሠ**
**በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት**
**የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር**

ምዕራባውያን "ሮም በአንድ ጀንበር አልተገነባችም" የተሠኘች አንዲት አባባል አለቻቸው፡፡ አባባሏ እድገት በድንገት የሚበቅል፣ ባሠቡበት ቅፅበት እውን የሚሆን ሳይሆን የራሱን ፍላጎት፣ ዕቅድ፣ ትግበራና ሂደት፣ አልፎ፣ በትግበራ የተገኙ ድክመቶችን ለመሻገር ሌላ ዕቅድ፣ ሌላ ተግባርና ሌላ ግምገማን የሚፈልግ፣ በስኬት የታዩ ተሞክሮዎችን በማጠናከር ወደፊት በፅናት መራመድን የሚሻ ረዥም የትግል ጉዞ መሆኑን አመላካች ነው፡፡

የኛም ቀደምት አበዎች ይህንኑ እውነታ ታሳቢ በማድረግ "ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሔዳል" በማለት "ቀስ ብሎ የመቸኮልን" ቀደምት ኢትዮጵያዊ እምነት አመላክተውናል፡፡

የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ዕድገት በሀገር ደረጃ ከ3 ሺህ ዓመታት የዘለቀ ታሪክ ቢኖረውም፤ በዘመናዊ አመራር ሒደት ከ100 ዓመታት ያለፈ ልምምድ ቢኖረንም ዛሬም በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ድርሻ 10 በመቶ እንኳን የማይደርስ ነው፡፡

ይህንን ለማሻሻል መንግሥት በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በርካታ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ሥራዎች ውስጥ አምራች ኢንተርፕራይዞችን ብቻ ለማስፋት የሚሠራ መንግሥታዊ የፌዴራል ተቋም (የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት) እንዲቋቋም ማድረጉ፣ ልዩ ልዩ ዘርፍ ተኮር የሆኑ የጥናትና ምርምር ተቋማት እንዲኖሩ ማስቻሉ፣ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የጥሬ ዕቃ ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችል ሀገራዊ አደረጃጀትን (የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ድርጅት) መፍጠሩ፣ የኢትዮጵያ ልማት ባንክን ጨምሮ በርከት ያሉ የመሥሪያና የማምረቻ መሣሪያዎችን በብድር የሚያቀርቡ ተቋማት እንዲበራከቱ ማድረጉና በወጪና ገቢ ንግዱ አካባቢ የሚስተዋሉ ችግሮችን የማበረታቻ ሥርዓቶችን በመዘርጋትና የአሠራር ሥርዓቶችን በማሻሻል እንዲፈቱ ማድረጉ እንዲሁም ዘርፉን ዋነኛ የሀገራዊ የኢኮኖሚ ሪፎርም ማዕከል ማድረጉ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

**«ሸማቹ ማኅበረሰብም ለሀገር ውስጥ ምርቶች ምንግዜም ቅድሚያ በመስጠት ኢትዮጵያዊ አምራቾችን በማበረታታትና የዜግነት ግዴታውን መወጣት የሚጠበቅበት ሲሆን፤ አምራቾችም የማይመጥኑ ምርቶችን በማምረት ሸማቾችን ሳስማሳዘን በከፍተኛ ሀገራዊ ኃላፊነት መሥራት ይገባቸዋል፡፡»**

ከዚህም በተጨማሪ መንግሥት ከውጪ በከፍተኛ ወጪ ያስገባቸው የነበሩና አዳዲስ የተፈጠሩ ልዩ ልዩ የኢንዱስትሪ ምርቶች ፍላጎቶችን በሀገር ውስጥ ካሉ አምራቾች ለመግዛት የፈጠረው ተነሳሽነት የዘርፉን ተጠቃሚነት እጅግ በከፍተኛ ደረጃ ያሳደገና ብዙዎች በአምራች ዘርፉ እንዲሠማሩ መነሳሳትን የፈጠረ ድጋፍ ሆኗል፡፡

በመቶ ሺዎች የሚቆጠር የትምህርት ቤት ዩኒፎርም፣ የመከላከያና የሚሊሻ አልባሳት፣ የተማሪዎች ጫማና መሠል ከፍተኛ የገበያ ትስስርን የሚፈጥሩ ምርቶች ዛሬ ላይ በሀገር ውስጥ አምራቾች አቅም እየተሸፈኑ ይገኛሉ፡፡ በቅርቡ ደግሞ የመንግሥትን የቢሮ መገልገያ ፈርኒቸሮች በሀገር ውስጥ አምራቾች ለማስመረት ከፍተኛ እንቅስቃሴዎች የሚከናወኑ ይሆናል፡፡ እነዚህ ውሳኔዎች በአንድ በኩል መንግሥት በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላርን ለውጪ አምራቾች እንዳያወጣ በማስቀረት የውጪ ምንዛሪ አቅማችንን በከፍተኛ ደረጃ ሲያሳድግ በሌላ በኩል የሀገር ውስጥ አምራቾችን የገበያ ትስስር በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን ያሳድጋል፡፡ በተራዛሚውም የኢኮኖሚ አቅማቸው ባደገበት መጠን ልክ የሥራ ዕድል ፈጠራ አቅማቸውን፣ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነታቸውንና የከፍተኛ ኃላፊነት ተሸካሚነታቸውን አቅም በማሳደግ የጥቅል የተወዳዳሪነት አቅማቸውን በእጅጉ የሚጨምረው ይሆናል፡፡

ከሰሞኑ በገንዘብ ሚኒስቴር አማካኝነት ከውጪ ለሚገቡ ምርቶች የዶላር አቅርቦት ላይ የተላለፈው ውሳኔ ለሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች በአንድ በኩል ከፍተኛ እድል፣ በሌላ በኩል ከፍተኛ ጫና ይዞ የመጣ ነው፡፡

ዕድልነቱ በተለይም በሀገር ደረጃ መመረት ለሚችሉ ምርቶች ከፍተኛ የገበያ አቅም መሆን መቻሉ ነው፡፡ ዛሬ ላይ እንኳን በከፍተኛ ካፒታል የተቋቋሙ ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ቀርቶ በአነስተኛና መካከለኛ ደረጃ የሚገኙ አምራች ኢንተርፕራይዞች በጥራትም በዋጋም መወዳደር የሚችሉ ሸቶዎችን፣ ምንጣፎችን፣ የሕፃናት መጫወቻዎችንና ከዚህ በፊት በሀገር ውስጥ የማይመረቱ የሚመስሉንን ቁሳቁሶች ማምረት ጀምረዋል፡፡ (በውል የሚታወቁትን የቢሮ ፈርኒቸሮች፣ የቦርሳና ዋሌቶች እንዲሁም የፍራፍሬ ጭማቂዎችን ያልጠቀስኩት አንባቢያን በሀገር ውስጥ ስለመመረታቸው በቂ ግንዛቤ አላቸው በሚል ነው)

በመሆኑም ይህንኑ ሀገራዊ እድል በአግባቡ ለመጠቀም በተለይም ሸማቹ በሌላ በኩል እንደሀገር የተሠጠንን እድል በጥራት ከደረጃ በታች፣ በዋጋ ውድ፣ በምቾት የማይመጥኑ ምርቶችን በማምረት የሀገር ውስጥ ሸማቾችን ላለማሳዘን አምራቾች በከፍተኛ ሀገራዊ ኃላፊነት መሥራት ይገባቸዋል፡፡

ሸማቹ ማኅበረሠብም ለሀገር ውስጥ ምርቶች ምንግዜም ቅድሚያ በመስጠት ኢትዮጵያዊ አምራቾችን ማበረታታትና ለቀጣይ ውጤታማ ሐገራዊ አቅማችን እድገት የዜግነት ግዴታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ለኢትዮጵያ ትንሳኤ እኛው የእኛው አቅም፤ እኛው የእኛው ብርታት መሆን ታሪካዊ ግዴታችን በመሆኑ ነው፡፡

ቴሌግራም፡t.me/ethiopianenterprisedevelopment
ፌስቡክ፡ www.facebook.com/ethiopianenterprisedevelopment